# በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

## የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

# የ1999 ዓ.ም የዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈጻጸም
# ግምገማ ሪፖርት

ሚያዝያ 1999
አዲስ አበባ

# በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

## የ1999 ዓ.ም የዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈጻጸም
## ግምገማ ሪፖርት

ሚያዝያ 1999
አዲስ አበባ

# ማውጫ

አርዕስት ገጽ


1 መግቢያ ............ 1
2 የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ ............ 3
2.1 የተፈጥሮ ሃብትና ግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት ............ 3
2.2 የቤተሰብ በጀትና ዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት ............ 5
2.3 የኢንዱስትሪ፣ንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት ............ 8
3 የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ፕሮጀክት ............ 9
3.1 3ኛው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራን በተመለከተ ............ 9
3.2 የቆጠራ ካርታ ሥራ እንቅስቃሴ ............ 13
3.3 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት ............ 13
3.4 የማህበራዊ ስታቲስቲክስ ጥናት ............ 16
4 የ1999 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም ............ 17
5 የሜቶዶሎጂን ሥራ በተመለከተ ............ 18
6 የመረጃ ማቀነባበርን ሥራ በተመለከተ ............ 20
7 የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን የማሻሻል ሥራን በተመለከተ ............ 21
8 የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ሥራን በተመለከተ ............ 24
9 የሕዝብ ግንኙነት፣ መረጃ ሥርጭትና ትምህርት ሥራን በተመለከተ ............ 28
10 የኦዲት ሥራን በተመለከተ ............ 30
11 የሕግ ሥራን በተመለከተ ............ 31
12 የፕላንና ፕሮግራም ሥራን በተመለከተ ............ 32
13 የሰው ሃብት ሥራ አመራር ሥራን በተመለከተ ............ 32
14 የፋይናንስ ሥራን በተመለከተ ............ 33
15 የቴክኒክና ንብረት አስተዳደር ሥራን በተመለከተ ............ 39
16 የሕትመት ሥራን በተመለከተ ............ 41
17 ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች ............ 41
18 ያጋጠሙ ችግሮችና የተሰጡ መፍትሄዎች ............ 42

# የ1999 ዓ.ም የዘጠኝ ወራት
# ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት

## 1. መግቢያ

መንግሥት የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ለሚያወጣቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፖሊሲዎች፣ እንደዚህም ፖሊሲዎችን መሠረት በማድረግ የታቀዱ የልማት ዕቅዶችን አፈጻጸም ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል ስታቲስቲካዊ መረጃ በየዘርፉ መገኘት ወሳኝነት አለው::

በዚህ ረገድ የማዕከላዊ ስታቲስቲክ ኤጀንሲ የሃገሪቱን የስታቲስቲክስ መረጃዎች ፍላጐት ለማሟላት በየጊዜው የመረጃ አሰባሰብ ስልቶችን በመቀየስ ልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መረጃዎች በማሰባሰብ፣ በማጠናቀርና በሪፖርት በማውጣት ለተጠቃሚዎች በማሰራጨት ላይ ይገኛል::

በ1999 በጀት ዓመትም በሁለት የተለያዩ ፕሮጀክቶች (የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮጀክትና የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ፕሮጀክት) ስር በርካታ ጥናቶችን ለማከናወንና በ1998 የመረጃ መሰብሰብ ተግባራቸው ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀላቸውንና በከፊል የመረጃ ቅንብር ሥራቸው የተጀመሩላቸውን ጥናቶች ለማጠናቀቅ እየሠራ ይገኛል:: በመሆኑም በበጀት ዓመቱ በአዲስ ዕቅድ እየተከናወኑ ያሉ፣

### 1.1 በተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮጀክት

#### 1.1.1 የግብርናና የተፈጥሮ ሃብትና ስታቲስቲክስ

- የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት፣
- የሰብል ምርት ናሙና ጥናት በመኸር ወቅት፣
  - የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት
  - የሰብል ምርት ናሙና ጥናት በመኸር ወቅት
  - የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ጥናት
- የሰፋፊ የግል፣ የመንግሥትና የድርጅት እርሻዎች ጥናት፣
- የቤት እንስሳት፣ የዶሮ ኃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች ጥናት፣

#### 1.1.2 የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ

- የግብርና ምርቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት፣
- የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት፣
- የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክሶች ዝግጅት፣
- ዓለም አቀፍ የዋጋ ንፅፅር ጥናት በአፍሪቃ (ቀጣይ ጥናት)፣

1.1.3 የኢንዱስትሪ፣ ንግድና ትራንስፖርት ስታቲስቲክስ

- የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣
- ወቅታዊ የማማረቻ ድርጅቶች ጥናት፣
- የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች የአምራቾች ዋጋ ጥናት፣
- የወጪ ንግድ ስታቲስቲክስ መረጃ ማሰባሰብና ማጠናቀር፣
- የትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ መረጃ ማሰባሰብና ማጠናቀር፣

1.1.4 ሌሎች ተጨማሪ ጥናቶች

- ከግብርና ወጪ በገጠር የሥራ መስክ ጥናት
- የምግብ ዋስትና ጥናት የመረጃ ቅንብር ሥራ

1.2 በሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ፕሮጀክት

1.2.1 የቆጠራ ቦታ ካርታ ዝግጅት ሥራን ማጠናቀቅ፣

1.2.2 የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ማካሄድ

- የስካኒንግ ሙከራ ቆጠራ ማካሄድ
- ለዋናው ቆጠራ የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶችን በማጠናቀቅ ቆጠራውን ማከናወን፣

1.3 ከ1998 ዓ.ም ወደ 1999 ዓ.ም በዕቅድ የተሸጋገሩ ጥናቶች

1.3.1 በግብርናና ተፈጥሮ ሃብት ስታቲስቲክስ

- የታረሰ መሬት ስፋትና የምርት መጠን ጥናት
- የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ጥናት
- የመሬት አጠቃቀም ጥናት
- የግብርና ምርት ናሙና ጥናት በበልግ ወቅት
- የሰፋፊና መካከለኛ የድርጅት እርሻዎች ጥናት

1.3.2 የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ

- የቤተሰብ ገቢ፣ፍጆታና ወጪ ጥናት መረጃ ቅንብርና የሪፖርት ዝግጅት፣

1.3.3 የሥነ-ሕዝብና ማህበራዊ ስታቲስቲክስ ጥናቶች

- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የባሕሪ ቅኝት ጥናት
- የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናት ናቸው።

ከላይ የተዘረዘሩትን ጥናቶች በበጀት ዓመቱ ለማከናወን መ/ቤቱ ከመንግሥት በተመደበ የካፒታል በጀት በተጨማሪ ከተለያዩ የልማት አጋሮች በተገኘ ፋይናንስ እንዲሁም በመ/ቤቱ

አማካይነት ጥናት እንዲሰራላቸው ከተጠየቁ መ/ቤቶች በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ባለው ቋሚና የኮንትራት ሰራተኞች በመታገዝና መርሃ-ግብር በማዘጋጀት ሥራዎቹን እያከናወነ ይገኛል:: በዚህ ሪፖርት ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ (ከሐምሌ 1 ቀን 1998 ዓ.ም እስከ መጋቢት 30 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ) የተከናወኑ ሥራዎች፣ የፋይናንስ አጠቃቀምና በሥራ ሂደት የታዩና በበላይ አካል ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ለማካተት ተሞክሯል::

## 2. የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ

### 2.1 የግብርናና ተፈጥሮ ሃብት ስታቲስቲክስ

#### 2.1.1 የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት

የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ከነሐሴ ወር 1998 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ እስከ ጥቅምት 15 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ ባሉት ቀናት ከመላው አገሪቱ በናሙና በተመረጡ የገጠር ቆጠራ ቦታዎች ላይ መረጃ ይሰበሰባል፤ ለዚህ ጥናት ባለፉት ዘጠኝ ወራት ይከናወናል ተብሎ በዕቅድ የተያዘው 93.25% ሲሆን፤ ይህም 100% ዕቅዱ በመከናወኑ የጥናቱ ውጤት ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል::

#### 2.1.2 የግብርና ናሙና ጥናት በመኸር ወቅት

በዚህ ጥናት ሥር ለታረሰ መሬት ስፋትና የምርት መጠን ጥናት ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ ለማከናወን የታቀደው 93.25% ሲሆን፤ ከዕቅዱ 86.3 % ፣ እንዲሁም የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ጥናትና የመሬት አጠቃቀም ጥናት 83.25% ለማከናወን ታቅዶ ከዕቅዱ 80.3% ሊከናወን ችሏል::

#### 2.1.3 የቤት እንስሳት፣ የዶሮ ሃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች ጥናት

በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት ላይ የቤት እንስሳት የዶሮ ሃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች ጥናትን ለማካሄድ በዕቅድ የተያዘው 93.25 በመቶ ሲሆን፤ ዕቅዱን ሙሉ በሙሉ 100 % ለማከናወን ተችሏል:: በመሆኑም የጥናቱን መረጃ በወቅቱ ለተጠቃሚዎች እንዲቀርብ ተደርጓል::

#### 2.1.4 የሰፋፊ የግል፣ የመንግሥትና የድርጅት እርሻዎች ጥናት

ለዚህ ጥናት ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለማከናወን በዕቅድ የተያዘው 74.92% ለማከናወን ሲሆን፣ እስካሁን ድረስ 50.25% ያህሉን ለማከናወን ተችሏል:: ይህም ከዘጠኝ

ወር ዕቅዱ 67.1% እንደሆነ ያመለክታል። ይህ ሊሆን የቻለውም በሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ፕሮጀክት ምክንያት የመርሃ - ግብር ለውጥ በመደረጉ ነው።

በሰፋፊ የግል፣ የመንግሥትና የድርጅት እርሻዎች ጥናት ለሚካተቱት የአበባ እርሻዎች መረጃ ለማሰባሰብ የሚያስችል ከእርሻው የሥራ ባህሪ ጋር የሚጣጣም መጠይቅና መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ዝግጅቱ ተጠናቆ አስተያየት እንዲሰጥበት ለሚመለከታቸው ክፍሎች ተሠራጥቷል።

### 2.1.5 ከ1998 ወደ 1999 ዓ.ም የተሸጋገሩና ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች

- የ1998 ዓ.ም የመኸር ወቅት በሰብል የተያዘ መሬት ስፋትና ምርት መጠን ጥናት፣ የእርሻ ሥራ ሁኔታ ጥናት እና የመሬት አጠቃቀም ጥናት ተጠናቀውና ሪፖርቶቹ ታትመው ለተጠቃሚዎች ተሰራጭተዋል።

- በ1998 የመረጃ መሰብሰቡ ተግባር የተጠናቀቀላቸው የበልግ ወቅት የመሬት ስፋትና ምርት መጠን ጥናት እንዲሁም የእርሻ ሥራ ሁኔታ ጥናት ተጠናቀው ሪፖርቶቹም ታትመው ለተጠቃሚዎች እንዲሠራጩ ተደርጓል።

- ለ1999 ዓ.ም. ለሚከናወኑ የሰብል ምርት ትንበያ፣ ለዋናው መኸር ወቅት የናሙና ጥናት፣ የቤት እንስሳትን የሚመለከቱ መረጃዎች ሊያስገኙ የሚችሉ መጠይቆችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ ውለዋል።

- በ1999 ዓ.ም. ለሚከናወነው ግብርና ጥናት በመስክ ሥራ ለሚሰማሩ ሠራተኞች በዋናው መ/ቤትና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በቂ ሥልጠና ተሰጥቷል። እንደዚሁም ለሰብል ትንበያ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና ቬሪፊኬሽን መመሪያ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ሠራተኞች ሥልጠና ተሰጥቷል።

- መ/ቤቱ በ1999 ለሚያዘጋጀው ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ጠቃሚ የሚሆኑ የግብርናና የተፈጥሮ ሃብት መረጃዎችን በማጠናቀር ለሚመለከተው ክፍል እንዲደርስ ተደርጓል።

- በሰኔ እና በሐምሌ ወር 1999 ዓ.ም ለሚካሄደው የበልግ ጥናት እንዲሁም ለ2000 የግብርና ናሙና ጥናት የሚያገለግሉ የመጠይቅና መመሪያ ዝግጅት እየተከናወነ ይገኛል።

## 2.1.6 ከግብርና ውጪ በገጠር የሥራ መስክ ጥናት

ይህ ጥናት የሚካሄደው ከዓለም ባንክ በተገኘው 99,962 ዶላር የበጀት ድጋፍ ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት ውስጥ የመስክ ሠራተኞች ስልጠና ተከናውኖ፤ የመረጃ መሰብሰቡ ሥራ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቋል:: እንዲሁም ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ኤዲቲንግና ኮዲንግ የማድረግ ተግባር እና ጥናቱ ከሚያካትታቸው አራት ክልሎች ውስጥ አንዱ የሆነውን የአማራ ክልል መረጃ የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራና መረጃ ወደ ኮምፒውተር የማስገባቱ ሥራ ተጠናቆ cleaned የሆነ መረጃ ለዓለም ባንክ ባለሙያዎች እንዲደርስ ተደርጓል:: ይህም ከዕቅዱ በአብዛኛው ቀድሞ ለመከናወን የተቻለ ነው::

## 2.1.7 የምግብ ዋስትና ጥናት

መ/ቤቱ ከምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ቢሮ ጋር በመተባበር የምግብ ዋስትና ጥናት ለማካሄድ በተደረገው ስምምነት መሠረት ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ዝግጅቶች ተጠናቀውና በመስክ መረጃ ተሰብስቦ በማጠናቀቅ የመረጃ ቅንብር ሥራ በማከናወን የተጣራ መረጃ (cleaned database) ለምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ቢሮ እንዲደርስ ተደርጓል::

## 2.1.8 የምግብ አቅርቦትና የሰብል ግምገማ

የመ/ቤቱ ባለሙያዎች ከFAO የምግብ አቅርቦትና የሰብል ግምገማ ቡድን ጋር በመሆን ለሦስት ሣምንታት የመስክ ግምገማ እንዲሳተፉ የተደረገ ሲሆን፤ የመስክ ግምገማው ውጤት ለ1999 ዓ.ም የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ማመሣከሪያነት መ/ቤቱ እንዲጠቀምበት ተደርጓል::

## 2.2 የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ

### 2.2.1 የዋጋዎች ጥናትና የዋጋ ኢንዴክስ

#### ሀ. በገጠር የግብርና ውጤቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት

የአምራቾች ዋጋ ጥናትን በተመለከተ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ ለማከናወን የታቀደው 67.37% ሲሆን፤ ዕቅዱን ሙሉ በሙሉ 100 % ለማከናወን ተችሏል:: ይኸውም ከሐምሌ ወር 1998 እስከ ህዳር ወር 1999 ዓ.ም ያለው ሪፖርት ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች የተሠራጨ ሲሆን፤ የታህሳስ ወር 1999 ዓ.ም ጥናት መረጃ ተቀነባብሮ ለህትመት ተልኳል፤ እንዲሁም የጥር ወር 1999 ዓ.ም መረጃ በመቀነባበር ላይ ይገኛል::

ለ. <u>ወርሃዊ የዕቃዎችና የአገልግሎት ዋጋ ጥናት</u>

በዚህ ጥናት ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ በዕቅድ ተይዞ የነበረው 60.41 % ሲሆን፤ የተከናወነው 60.41% ወይም የዕቅዱ 100 % ነው:: በመሆኑም ከሐምሌ 1998 እስከ ኅዳር ወር 1999 ዓ.ም ያለው ሪፖርት ታትሞ ለተጠቃሚዎች የተሰራጨ ሲሆን፤ የታህሳስ ወር 1999 ዓ.ም መረጃ ደግሞ ተቀነባብሮ ለህትመት ተልኳል::

ሐ. <u>ወርሃዊ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ</u>
<u>የአገር አቀፍና የክልሎች</u>

የአገር አቀፍና የክልሎች የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ ከሐምሌ ወር 1998 እስከ የካቲት ወር 1999 ዓ.ም ድረስ ያለው በየወሩ ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ተደርጓል:: የመጋቢት ወር 1999 ዓ.ም አሃዝ እየተቀነባበረ ይገኛል::

እንዲሁም የአዲስ አበባ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ አሃዝ ከሐምሌ ወር 1998 ዓ.ም እስከ የካቲት ወር 1999 ዓ.ም ድረስ ያለው በየወሩ ተቀነባብሮና ታትሞ ለተጠቃሚዎች በወቅቱ እንዲደርስ የተደረገ ሲሆን፤ የመጋቢት ወር 1999 ዓ.ም አሃዝ እየተቀነባበረ ይገኛል::

መ. <u>ከ1998 ወደ 1999 ዓ.ም. የተሸጋገሩ ሥራዎች</u>

የሰኔ ወር 1998 ዓ.ም. የአገር አቀፍ፣ የክልሎችና የአዲስ አበባ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ በ1999 ዓ.ም. የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ተቀነባብሮና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል::

ሠ. <u>የዓለም አቀፍ ንፅፅር መረሃ - ግብር በአፍሪካ</u>

- ይህ ጥናት በአፍሪካ ልማት ባንክና በምሥራቅና ደቡብ አፍሪካ የንግድ ቀጠና ጋር በመተባበር የሚካሄድ ነው:: በመሆኑም በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት መረጃ ወደአፍሪካ ልማት ባንክ የተላከ ሲሆን፤ የሁለተኛው ሩብ ዓመት መረጃ የዳታ ኤዲቲንግ፣ ኮዲንግ፣ ኢንትሪ፣ ቬሪፊኬሽንና የቫሊደሽን ተግባር በመከናወን ላይ ይገኛል:: እንዲሁም የሶስተኛው ሩብ ዓመት መረጃም የኢዲቲንግ ኮዲንግ ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል::

- የዚህ ጥናት አካል የሆነው የመድሃኒቶች ዋጋ መረጃ የመሰብሰብ ሥራ በየሩብ ዓመቱ ማለትም በነሐሴ ወር 1998 ዓ.ም፣ በኅዳር ወርና በመጋቢት 1999 ዓ.ም ተከናውኗል::

### 2.2.2 የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት

በ1997/98 በሁለት ዙር የመረጃ መሰብሰብ ተግባር የተጠናቀቀለት የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት መረጃ የመገምገም ሂደት በኤጀንሲው ተጠናቆ ጥሬ መረጃው ጥልቅ ትንተና እንዲካሄድበት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ተልኳል:: እንዲሁም በተዘጋጀው የሠንጠረዥ መርሃ ግብር መሠረት ሪፖርት የማውጣት ተግባርና የመረጃው ውጤት ትንተና እየተከናወነ ሲሆን፣ የጥናቱ ሪፖርትም በሚቀጥሉት ሁለት ወራት ታትሞ ለተጠቃሚዎች ይሰራጫል::

### 2.2.3 ልዩ ልዩ ሥራዎች

- የአምራቾች ዋጋ ጥናትና ለወርሃዊ የዕቃዎችና የአገልግሎቶች ዋጋ ጥናት የመረጃ አሰባሰብ መመሪያ በማዘጋጀትና ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መጠይቅ በማዘጋጀት ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲደርስ ተደርጓል::

- በአዲስ መልክ ለሚዘጋጀው የሸማቶች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ የሚያገለግል በ1996/97 የተጠናውን የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናትን መሠረት በማድረግ አዳዲስ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን በመምረጥ ከህዳር ወር 1999 ዓ.ም ጀምሮ መረጃዎች እንዲሰበሰቡ የመረጃ ማሰባሰቢያ ቅጽ ተዘጋጅቶ ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ተሠራጭቷል::

- በአስራ አንድ ክልሎች ለኢንዴክስ ዝግጅት የሚያገለግል የ1996/97 ዓ.ም የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናትን መሠረት ያደረገ የዕቃና አገልግሎቶች ማዕቀፍ የመምረጥና ለየክልሉ በተመረጡ ዕቃዎች የመነሻ ዋጋቸውን የማጥናትና የመወሰን ሥራ ተጠናቋል:: አጠቃላይ የአሠራር ሁኔታ የሚያብራራና የሚገልጽ ሜቶዶሎጂ እንዲሁም ለአገር አቀፍ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ ለማዘጋጀት የሚረዳ የExpenditure Weight Matrix ተዘጋጅቷል::

- በቤተሰብ ፍጆታና ወጪ ጥናት ውስጥ ማካተት ያለባቸው የዕቃዎችና አገልግሎቶች ዝርዝር መረጃ ለማሰባሰብ በሚያስችል መልኩ መጠይቆች ተዘጋጅተው መረጃው እንዲሰበሰብ ተደርጓል:: የጥናቱ ውጤትም ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ መሆን ስላለበት የዕቃዎችና የአገልግሎቶችን የማዋቀር ተግባር ተካሄዶ ሪፖርት የማውጣት ሥራ ተጠናቋል::

## 2.3 የኢንዱስትሪ፣ ንግድ ትራንስፖርት መገናኛ ስታቲስቲክስ

### 2.3.1 የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ ጥናቶች

- የወቅታዊ የማምረቻ ድርጅቶች ጥናትን በተመለከተ ባለፉት ዘጠኝ ወራት 65.75% ለማከናወን ታቅዶ፤ የተያዘው ዕቅድ 100% የተከናወነ ሲሆን፤ በዚህም የመጀመሪያውና የሁለተኛው ሩብ ዓመት የጥናቱ ሪፖርት ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

- የተፈበረኩ ዕቃዎች የአምራቾች ዋጋ ጥናትን በሚመለከት በዘጠኝ ወራት ውስጥ ለማከናወን በታቀደው 65.75% ሲሆን፤ ዕቅዱን ሙሉ በሙሉ ለማጠናቀቅ ተችሏል።

- የ1998 ዓ.ም መረጃን የሚያመለክተው የትላልቅና መካከለኛ የኢንዱስትሪዎች ጥናትን በሚመለከት በዘጠኝ ወራት ውስጥ ለማከናወን የታቀደው 60.0 ሲሆን፤ 60.0 ዕቅዱ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል። በዚህ መሠረት የጥናቱ መረጃ ሙሉ በሙሉ ከመስክ ተሰብስቧል።

- የውጭ ንግድ መረጃን በተመለከተ በመረጃው ላይ ይታዩ የነበሩ ችግሮችን ከ Comesa ጋር በመተባበር ችግሩን በማስወገድ በአሁኑ ወቅት እስከ Feb. 2007 ያለውን የውጭ ንግድ መረጃ ለተጠቃሚዎች ማቅረብ በሚያስችልበት ደረጃ ላይ ይገኛል።

### 2.3.2 ከ1998 ወደ 1999 የተሸጋገሩና ሌሎች ሥራዎች

- ከApril 2006-June 2006 ድረስ ያለው የአምራቾች ዋጋ ኢንደክስ ሥራ ተጠናቆ ሪፖርቱ ተዘጋጅቶና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

- የ1997 ዓ.ም መረጃ የሚያመለክተው የትላልቅና መካከለኛ የኢንዱስትሪዎች ጥናት መረጃ ተጠናቅሮና ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- በ1998 በጀት ዓመት የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር የተጠናቀቀለት የአነስተኛ ማምረቻ ድርጅቶች ጥናት ሪፖርት ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች እንዲሠራጭ ተደርጓል።

- ለበርካታ ተጠቃሚዎች መረጃ የመስጠት ሥራ ተከናውኗል።
- ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት (STATISTICA ABSTRACT) ይህ መጽሔት በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በሥነ-ሕዝብ ዘርፎች ሁሉ መረጃዎች ተጠቃለው የሚወጡበት ሲሆን መጽሔቱ በዕቅዱ መሠረት ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

## 3. የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ፕሮጀክት

### 3.1 3ኛው ሕዝብና ቤቶች ቆጠራን በተመለከተ

ለሦስተኛ ጊዜ በመላው አገሪቱ በግንቦት ወር 1999 ዓ.ም ለሚካሄደው አገር አቀፍ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ባለፉት ዘጠኝ ወራት የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል:: ሥራዎቹ በአብዛኛው ካለፉት ዓመታት ቀጣይነት ያላቸው ሲሆኑ፤ በበጀት ዓመቱ በቆጠራው መረጃ የመሰብሰቡ ሂደት የሚጠናቀቅበት ጊዜ በመሆኑ የቆጠራው ሥራ እንቅስቃሴዎች በዚህ በጀት ዓመት ከሌላው ጊዜ በተለየ ሁኔታ ጐላ ብለው የሚታዩበት ወቅት ነው ማለት ይቻላል:: በዚሁም መሠረት ከሐምሌ 1 ቀን 1998 ዓ.ም እስከ መጋቢት 30 ቀን 1998 ዓ.ም ዋና ዋና የቆጠራ ተግባራት አፈጻጸም እንደሚከተለው ቀርበዋል::

#### 3.1.1 የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የሎጂስቲክስ ዝግጅትን በተመለከተ

የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ሥራን ለማከናወን የተለያዩ የሎጂስቲክስ ዝግጅቶች ማድረግ አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም:: በመሆኑም በየደረጃው ለሚከናወኑ የቆጠራው የቅድመ ዝግጅት ተግባራት የሎጂስቲክስ አቅርቦት የተሟላ የማድረግ ሥራ የተጀመረው ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን፤ በተለይም ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከመንግስት በተመደበ በጀት እና ከለጋሽ ድርጅቶች በተገኘ የዕርዳታ ገንዘብ ለቆጠራው አገልግሎት በርካታ ቁጥር ያላቸው የተለያዩ ቁሣቁሶች ተገዝተው ተዘጋጅተዋል:: ይሄውም ለቆጠራው መረጃ ማቀነባበሪያ የሚውሉ 11 ስካነሮች፣ የተለያዩ የጽ/መሣሪያዎች፣ ኮምፒውተሮች፣ የቆጣሪ ቦርሣዎች ወዘተ... ግር ከተባበሩት መንግሥታት የሥነ- ሕዝብ ፈንድ፣ ከተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅት ኔዘርላንድ እና ከአየር ላንድ መንግሥታት በተገኘው የገንዘብ ዕርዳታ ተከናውነዋል::

በአጠቃላይ ለቆጠራው አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ ቁሣቁሶች ግዥ በአሁኑ ወቅት ሙሉ በሙሉ ተከናውኖ ከቆጠራው መጠይቆች፣ ቅጾች፣ መመሪያዎች፣ ወዘተ... ጋር በማቀናጀት ወደተለያዩ አካባቢዎች ለማሰራጨት የማደራጀቱ ሥራ ተጠናቋል::

#### 3.1.2 የፋይናንስ አፈፃፀም መመሪያ ዝግጅት

የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሰው ኃይልና ቁሣቁስ የሚጠይቅ ግዙፍ ሥራ በመሆኑ ሥራውን ለማስፈፀም የሚያስፈልገው ገንዘብም እንዲሁ ከፍተኛ ነው:: ስለሆነም ለቆጠራው ሥራ ማስፈፀሚያ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ወደየክልሎቹ /አዲስ አበባና ድሬዳዋን ጨምሮ/ የሚሰራጭ በመሆኑ በሁሉም አካባቢ ሕግንና ደንብን በተከተለ መንገድ ሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ አንድ ወጥ የፋይናንስ አፈፃፀም መመሪያ ማዘጋጀት ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል:: በዚሁም መሠረት ቀደም ሲል ከተካሄዱት ተመሣሣይ

ቁጠራዎች የተገኙ ልምዶችንና ተሞክሮዎችን እንዲሁም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ዘርፎች በተገኙ ሙያዊ እገዛ ለቆጠራው የፋይናንስ አፈፃፀም መመሪያ ተዘጋጅቶ በየክልሉ እየተሠራጨ ይገኛል።

በተጨማሪም በቆጠራው የፋይናንስ ሥራ ላይ በተግባር የሚሳተፉ የሥራ ኃላፊዎችና የሂሳብ ባለሙያዎች በዋናነት በመመሪያው አጠቃቀምና የቆጠራው የፋይናንስ አፈፃፀም ላይ ግልጽና በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሂሳብ ባለሙያዎች ጋር በመተባበር ለክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎችና የሂሳብ ባለሙያዎች አዲስ አበባ ላይ የአንድ ቀን ሥልጠና ለመስጠት ታቅዷል። በተመሳሳይ እዚህ ሥልጠና የሚወስዱ ባለሙያዎች በክልላቸው በየደረጃው በቆጠራው የበጀት አፈፃፀም ሥራ ላይ ለሚሳተፉ የሂሳብ ኃላፊዎችና የሂሳብ ባለሙያዎች ሥልጠና እንደሚሰጡ ይጠበቃል።

### 3.1.3 ስለቆጠራው የትምህርትና ቅስቀሣ ተግባርን በተመለከተ

የአገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል የሚመለከት በመሆኑ ከእያንዳንዱ ተገቢውን ድጋፍና ትብብር ለማግኘት፣ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ትክክለኛ ምላሽ ለማግኘት እና የሚሰበሰበው መረጃ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን እንዲሁም አጠቃላይ ሥራዎች በተገቢው ፍጥነትና በተፈቀደው በጀት ያለምንም ችግር ለማከናወን ስለቆጠራው ዓላማ፣ ጥቅሞች፣ ወዘተ... ለማስመዝገብ ሰፊ ትምህርትና ቅስቀሳ ማካሄድ ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ ባለፉት ዘጠኝ ወራት የተለያዩ የትምህርትና ቅስቀሳ ቁሳቁሶች ተዘጋጅተዋል። ይኸውም አንድ ወጥ ወይም ተመሳሳይ ግንዛቤ በሁሉም ዘንድ እንዲኖር የሚያግዝ የቆጠራው የትምህርትና ቅስቀሳ መሪ ሰነድ ተዘጋጅቷል።

በተጨማሪም ፖስተሮች፣ ብሮሸሮች/በራሪ ጽሑፎች፣ ድራማዎች፣ ግጥሞች፣ መዝሙሮች፣ በጋዜጦች የፊትና የውስጥ ገጾች ሊታተሙ የሚችሉ የተለያዩ ትምህርታዊ ጽሑፎች፣ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራዎች አፈፃፀምና የቅስቀሳ ማቴሪያሎች አጠቃቀም መመሪያና የመሳሰሉት የትምህርትና ቅስቀሳ መንገዶችን በመጠቀም ስለ ቆጠራው በስፋት ትምህርትና ቅስቀሳ ለማድረግ ዝግጅቱ ተጠናቆ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል ።

ከእነዚህም ሌላ ስለቆጠራው ዓላማ፣ ጥቅሞች፣ ወዘተ ... ላይ በመመርኮዝ የተለያዩ ጥናታዊ በማዘጋጀት ሥራዎች በተለያዩ መድረኮች በየደረጃው ለሚገኙ የሥራ ኃላፊዎችና የኅብረተሰብ ክፍሎች ተገቢው የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራዎች ተሰርተዋል። ከእነዚህም ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል በአዲስ አበባ ከተማ 500 ለሚደርሱ የቀበሌ አመራር አካላትና ሕዝባዊ ድርጅቶች የግማሽ ቀን ሴሚናር ተሰጥቷል። እንዲሁም በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በኦሮሚያና በጋምቤላ የሥነ-ሕዝብና

ስታቲስቲክስ ቢሮዎች በተዘጋጁ ሴሚናሮች ላይ በመገኘት ስለቆጠራው ዓላማ፣ ጥቅምና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ገለፃዎች ተደርገዋል።

በተጨማሪም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ መምሪያ ለጋዜጠኞች በተሰጠ ሴሚናር ላይ ቆጠራውን አስመልክቶ የአንድ ቀን ትምህርት ተሰጥቷል። እንዲሁም ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በመስከረም ወር 1999 ዓ.ም. ላይ በተደረገ የፕላዝማ የትምህርት ጉባኤ ላይ ለተሳተፉ መምህራን ስለቆጠራው አጠቃላይ ሁኔታና መምህራን በሦስተኛው ዙር ግንዛቤ እንዲኖራቸው ሰፊ ማብራሪያና ገለፃ ተደርጓል። በተጨማሪም ለብዙሃን መገናኛ ባለሙያዎችና ጋዜጠኞችም ግማሽ ቀን ሴሚናር ተካሂዷል።

### 3.1.4 ለቆጠራው የገንዘብና ሌሎች ድጋፎችን ማፈላለግን በተመለከተ

የቆጠራው ውጤት ዋነኛ ተጠቃሚ መንግሥትና ሕብረተሰቡ ቢሆንም መንግስታዊ ያልሆኑና ዓለም አቀፍ ድርጅቶችም የቆጠራውን ውጤት ተጠቃሚ ናቸው። በመሆኑም የቆጠራውን በጀት በከፍተኛ መጠን እየደገፈ ያለው መንግሥት ሲሆን፤ ተጠቃሚ የሆኑ ሌሎች አካላትም ድጋፍና ትብብር እንደሚያደርጉ ይጠበቃል። ስለዚህ ስለቆጠራው አጠቃላይ ስትራቴጂና የአፈፃፀም ዕቅድ /Strategy and Implementation Plan/ ተዘጋጅቶ ለለጋሽ ድርጅቶችና ሌሎች አካላት በማሰራጨትና ተገቢ ማብራሪያዎች በመስጠት ለጋሽ ድርጅቶችን በአንድ የጋራ መድረክ ላይ በመጋበዝ፣ በማነጋገርና አስፈላጊ ማብራሪያዎችን በመስጠት ለቆጠራው ማስፈፀሚያ ድጋፍና ትብብር ለማሰባሰብ ጥረት ተደርጓል።

በተደረገው ጥረት መሠረትም እስከአሁን ከተባበሩት መንግሥታት የሥነ-ሕዝብ ፈንድ (UNFPA) 2,039,200 ዶላር (የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ ከተጀመረ ጀምሮ)፣ ከተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅት (UNDP) 2,300,000 ዶላር፣ከአየር ላንድ መንግሥት 144,000 ዶላር ከኔዘርላንድ መንግሥት 42,000 ዶላር ከተባባሩት መንግሥታት የሕፃናት መርጃ ድርጅት (UNICEF) 200,000 ዶላር በጠቅላላው 4,725,220 ዶላር የተገኘ ሲሆን፤ በተጨማሪም ከሚቀጥለው በጀት ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ የሚሆን የእንግሊዝ መንግሥት የልማት ድርጅት (DFID) እንደ ኢ.አ ከ2007-2011 ለሚደረጉ የቆጠራ ተግባራት (በሶማሌ ክልል የሚካሄደውን ለሣተላይት ኢሜጀሪ ሥራ ጨምሮ) 7 ሚሊዮን ፓውንድ ተገኝቷል።

### 3.1.5 የቢሮና የመጋዘን ችግርን በተመለከተ

ኤጀንሲው ያለበትን የቢሮና የመጋዘን ችግር ለማቃለል ላለፉት ተከታታይ ዓመታት በመንግሥት በኩል መፍትሄ እንዲሰጠው ጥያቄ ማቅረቡ ይታወቃል። በተለይም ደግሞ በቅርብ ጊዜ ውስጥ የሚካሄደው 3ኛው አገር አቀፍ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ከግዙፍነቱ በተጨማሪ ለሥራው የሚደረገው አጠቃላይ ዝግጅት ሰፊ በመሆኑ ቆጠራው እስከሚጠናቀቅ ድረስ (ለሁለት ዓመት ተኩል ያክል) የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤትን እንዲጠቀምበት ተወስኖ ሥራው እየተካሄደ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪ መንግስት ኤጀንሲው አዲስ ቢሮ እንዲገነባ በመፍቀዱ ለግንባታው ሥራ የተለያዩ የዝግጅት ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

### 3.1.6 የቆጠራ ቁሳቁስ የማደራጀትና የማሰራጨት ሥራ ክንዋኔን በተመለከተ

በቆጠራው ሥራ ላይ የሚሳተፉ ሠራተኞች በጣም ብዙ በመሆናቸውና መረጃ የሚሰበሰብለት ሕዝብ ብዛት በጣም ከፍተኛ በመሆኑ እጅግ በጣም ቁጥር ያላቸው የተለያዩ የቆጠራ መጠይቆች፣ ቅጾች፣ መመሪያዎች፣ የጽሕፈት መሣሪያዎች፣ ወዘተ ... በቆጠራ ቦታዎች ብዛት ልክና በሥልጠና ማዕከላት ብዛት መጠን የማደራጀት ሥራ በርካታ የሰው ኃይልና ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ሥራ ነው። ስለሆነም ከ200 በላይ ቋሚና ኮንትራት የኤጀንሲው ሠራተኞችን በመመደብ ከየካቲት ወር 1999 ዓ.ም ጀምሮ የማደራጀቱ ሥራ ሲካሄድ ቆይቶ በተደረገው ስልታዊና የተቀናጀ የቁጥጥርና የክትትል ሥራ ከተያዘለት ጊዜ ለደም ብሎ ማለትም ከመጋቢት 30 ቀን 1999 ዓ.ም በፊት ከሞላ ጎደል /ከፊል የሦስተኛ ዙር ሥልጠና ቁሳቁስ ብቻ ሲቀር/ ተጠናቋል።

ከላይ በተገለጸው መልክ በሺህዎች በሚቆጠሩ ትላልቅ ካርቶኖች የተደራጁ የቆጠራ ቁሳቁስን ወደተለያዩ አካባቢዎች ለማሰራጨት በርካታ ከባድና መካከለኛ የጭነት ካሚዮኖች ያስፈልጋሉ። ስለሆነም እነዚህን ቁሳቁሶች ቀደም ብሎ ወደተለያዩ ዞኖች ለማሰራጨት ይቻል ዘንድ የየትኞቹ ዞኖች ቁሳቁስ ከየትኛው ሌላ ዞን ጋር ሊጓጓዝ እንደሚችል በጥንቃቄ ከተጠና በኋላ በ31 የጉዞ መስመሮች ዕቃዎቹን ለማጓጓዝ ዝግጅቱ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል። በዚህ ረገድ ወደየአቅጣጫው ለማጓጓዝ የሚያስፈልጉ ተሽከርካሪዎችን በኪራይና በትብብር ለማግኘት የሚያስችሉ ስልቶች ተቀይሰዋል። ይኼውም አብዛኛው የጉዞ መስመሮች በኪራይ በሚገኙ የጭነት መኪኖች ይሸፈናሉ ተብሎ ስለተገመተ አስቀድሞ ጨረታ ወጥቶ ሂደቱ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ የተቀሩትን በትብብር ከየመ/ቤቱ ለማግኘት እንዲቻል በርከት ያሉት በደብዳቤ ተጠይቀው ከተወሰኑ መ/ቤቶች ጥሩ ምላሽ ተገኝቷል። በዚሁም መሠረት የቆጠራውን ቁሳቁስ ከሚያዝያ አጋማሽ ጀምሮ ለማጓጓዝ አስፈላጊ ሁኔታዎች ተመቻችተዋል።

### 3.2 የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ እንቅስቃሴ

ሦስተኛውን የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ለማከናወን በቅድሚያ መሠራት ካለባቸው ተግባራት ውስጥ አንዱና ዋነኛው የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ ነው፡፡ የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ ዋነኛው ዓላማ በቆጠራ ወቅት ማንኛውም ሰው/ቤት ሳይቆጠር እንዳይቀርና ከአንድ ጊዜ በላይ እንዳይቆጠር ለመከላከል የሚያስችል የቆጠራና የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታዎችን ማዘጋጀት ነው፡፡ በመሆኑም ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ 10,451 የቆጠራ ቦታ ካርታ የተካሄደ ሲሆን፣ ካለፉት ዓመታት ጀምሮ እስከ መጋቢት 30/1999 ዓ.ም ድረስ በአጠቃላይ 83,193 ቆጠራ ቦታ ካርታ /አፋር ክልል ጭምር/ በሁሉም ክልሎች/ መስተዳድሮች ተጠናቋል፡፡ በአሁኑ ወቅት የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራው ተጠናቋል፡፡

### 3.3 ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች

#### 3.3.1 የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የሙከራ ጥናት

የ1999 ዓ.ም የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃን አዲሱን የስካኒንግ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ለማቀነባበር በታቀደው መሠረት ለስካኒንግ ምቹ ሆነው የተዘጋጁትን መጠይቆች ግልፅነት፣ የአቀራረብ አመቺነት፣ የመጠይቆቹ የአያያዝ ጥንቃቄ፣ ወዘተ ... ለመፈተሽ ኩሉም አካባቢ በተመረጡ 100 የቆጠራ ቦታዎች ሁለተኛውን ዙር የሙከራ ቆጠራ ለማካሄድ የሚከተሉት ተግባራት ተከናውነዋል:-

- በስካኒንግ የሚቀነባበሩ መጠይቆች ይዘት ቀደም ሲል ከተዘጋጁት መደበኛ መጠይቆች ጋር አንድ ቢሆኑም የጥያቄዎችና የመልስ አማራጮች አቀማመጥ፣ የመልስ አሞላል ሁኔታ፣ መጠይቆቹ የሚታተሙበት ወረቀት መጠንና ጥራት የተለዩ ስለሆነ በተለመደው (Conventional) የቆጠራ አሠራር ስልት መሠረት የተዘጋጁትን መጠይቆች እንዳለ ለስካኒንግ መረጃ ቅንብር ሥራ መጠቀም ስለማይቻል ከኮሚሽኑ ጽ/ቤት /ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ/ አንድ ከፍተኛ ባለሙያ መጠይቆቹንና ቅፆቹን በአማርኛ እንዲያዘጋጁና በሂደቱም ተፈላጊውን እገዛ እንዲያደርጉ ወደ እንግሊዝ አገር ተልከው ስካነሮችን በማምረትና መጠይቆችን ዲዛይን በማድረግ እንዲሁም በሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ከፍተኛ ልምድ ያካበተውና በአገራችንም ከብሔራዊ ፈተናዎች ድርጅት ጋር ከአሥራ አምስት ዓመት በላይ በመስራት ላይ ካለው DRS ከተባለ የእንግሊዝ ድርጅት ጋር በመሆን ለስካኒንግ ምቹ የሆኑ መጠይቆችንና ቅፆችን የማዘጋጀት ሥራ ተከናውኗል፡፡

- ከነሐሴ 8 - 19/1998 ዓ.ም ድረስ ከየክልሉ ለቆጣሪነትና ለተቆጣጣሪነት ለተመለመሉ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ መምህራን የክፍል ውስጥ ገለፃ እና የመስክ የተግባር ልምምድ አካቶ የያዘ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

- ሥልጠናው እንደተጠናቀቀም ሠልጣኞች ወደየመጡባቸው ክልሎች በመመለስና በናሙናነት በተመረጡ አንድ መቶ የቆጠራ ቦታዎች በመሠማራት ከነሐሴ 25/1998 እስከ ጳጉሜ 5/1998 ድረስ በስካኒንግ የሚቀነባበሩ መጠይቆችን በመጠቀም የሙከራ ቆጠራ አከናውነዋል በመስጠት የሙከራ ቆጠራው ተካሄዷል፡፡

- የሙከራ ቆጠራው በሚካሄድበት ወቅት የሚመለከታቸው ባለሙያዎች በመስክ በመገኘት የታዩ ችግሮችንና ጠንካራ ጐኖች በመለየት ሪፖርት ቀርቧል፡፡ የሙከራ ጥናቱ የመረጃ ቅንብር ተካሄዶ ለዋናው ቆጠራ መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎችና ማሻሻያዎች ተለይተዋል፡፡

- በዋናው ቆጠራ ለሚደረገው ስልጠና እንዲረዳ በሙከራ ቆጠራው ላይ የተሣተፉ መምህራን (ቆጣሪና ተቆጣጣሪዎች) ጋር ውይይት በማድረግ ለስልጠና ዝግጅቱ ጠቃሚ ማሻሻያዎች ተገኝተዋል፡፡

### 3.3.2 የቆጠራ መጠይቆች ሕትመት

የቆጠራው መጠይቆችና ቅጾች የሚታተሙት በእንግሊዝ አገር በዲ.አር.ኤስ ድርጅት አማካኝነት ሲሆን፤ የሕትመቱ ሥራ ከህዳር 24 ቀን 1999 ዓ.ም. ጀምሮ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ መጠይቆቹ ታትመው ከተጠናቀቁ በኋላ በቅደም ተከተል በ3 ዙሮች ወደ አገር ወስጥ የገቡ ሲሆን፤ መጠይቆች አገር ውስጥ ለማሣተም ያልተቻለው መጠይቆቹን ለስካኒንግ መሣሪያ በሚመች መንገድ ዲዛይን የሚያዘጋጅ ልምድ ያለው የሕትመት ድርጅት በአገር ውስጥ ባለመኖሩና ስካነሮቹ በተመረቱበት እንዲሁም የመጠይቆች ሕትመትና ዲዛይን የሚዘጋጅበት ተመሣሣይ ድርጅት ሲሆን በሥራ ሂደት ለሚያጋጥሙ ችግሮች አስቸኳይ መፍትሔ ለማግኘት ሲባል ነው፡፡

### 3.3.3 የቆጣሪዎችንና የተቆጣጣሪዎችን መመሪያ ማሻሻልና ማተም

በቆጠራው የሚሰበሰቡ መረጃዎች የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው አንድ ወጥ በሆነ የአሠራር መመሪያ እንዲሰበሰቡ በሥራው ላይ ለሚሳተፉ ሠራተኞች መመሪያ ማዘጋጀት ግዴታ ነው፡፡ በመሆኑም ቀደም ሲል ተዘጋጅተው የነበሩ የቆጣሪዎችና የተቆጣጣሪዎች መመሪያን በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉት የሙከራ ቆጠራዎች በተገኙና በተደረጉ ግምገማዎች የተሰጡ አስተያየቶችን በማካተት ሁለት ጊዜ ማሻሻያ ተደርጐባቸውና ለስካኒንግ የተዘጋጁ መጠይቆችንና ቅጾችን ለመሙላት በሚያስችል መንገድ ተዘጋጅተው የሕትመት ሥራቸው ተጠናቋል፡፡

### 3.3.4 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን አካላት ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነትን ማዘጋጀት

ሦስተኛውን የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ በተሟላ ሁኔታ ጀምሮ ለመጨረስ እንዲቻል ከክልል አንስቶ እስከ ወረዳ መስተዳድር ደረጃ ለሚቋቋሙት የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽኖች እንዲሁም በገጠርና በከተማ ቀበሌዎች ደረጃ ለሚቋቋሙት የቆጠራ ኮሚሽኖች ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት ተዘጋጅተዋል። የተዘጋጀው ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት ለመፈፀም በሚያስችልና በእያንዳንድ ኮሚሽን ስር ለሚደራጁ አካላት ማለትም ለትምህርትና ቅስቀሳ፣ የቆጠራ ጽ/ቤት ኃላፊ፣ ቆጠራ የመስክ የቴክኒክ አገልግሎት ኃላፊ፣ የፋይናንስ እንዲሁም የኦዲተሮች በሚመለከት ሲሆን፤ በየደረጃው በሚገኙ ባለሙያዎችና የአመራር አባላት ተገምግሞና የመጨረሻ መልክ እንዲይዝ ተደርጎ በበቂ ኮፒ ታትሞ በየክልሉ ለተቋቋሙ ኮሚሽኖች እንዲሰራጭ ተደርጓል።

### 3.3.5 የቆጠራውን ውጤት ለማቅረብ የሚችል የታቡሌሽን ዕቅድ /Tabulation Plan/ ማዘጋጀት

በቆጠራው በርከት ያሉ የሥነ-ሕዝብ፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን እንዲሁም በአገሪቱ የሚገኙ ቤቶች ሁኔታን የሚያንፀባርቁ መረጃዎች ለመሰብሰብ ታቅዷል። በመሆኑም እነዚህ የተሰበሰቡ መረጃዎች በሦስት የተለያዩ ሪፖርቶች ማለትም የተለያዩ መረጃዎችን የያዙ ሠንጠረዦች በስታቲስቲካል ሪፖርት /Statistical Report/ እንዲሁም የትንተና ሠንጠረዦች ሪፖርት / Analytical Report / በተጨማሪም እነዚህን ሁለት ሪፖርቶች ጠቅለል በማድረግና ለውሣኔ ሊረዱ የሚችሉ ግልጽና ቀላል አቀራረብ ያላቸው ማጠቃለያ ሪፖርቶች /Summary Report/ ለማዘጋጀት ታቅዷል። ስለዚህ የተለያዩ ሪፖርቶች ለማዘጋጀት የሚረዱ **150** የተለያዩ የሠንጠረዥ ዓይነቶችን የያዘ ታቡሌሽን ፕላን ተዘጋጅቷል።

### 3.3.6 የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን በክልሎች ስለመቋቋሙ

የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽንን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር **449/1997** ለአገር አቀፉ ኮሚሽን በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሠረት በኮሚሽኑ አንደኛ ስብሰባ የአገሪቷን የአስተዳደር እርከኖችን ተከትሎ ኮሚሽኖች በየደረጃው እንዲቋቋሙ ውሳኔ አስተላልፏል።

ይህንኑ ውሳኔ መሠረት በማድረግ ኮሚሽኖች የሚኖራቸውን ተግባርና ኃላፊነት በዝርዝር በማዘጋጀትና ሌሎች መሰናዶዎችን በማድረግ የክልል ኮሚሽኖችን ለማቋቋም አመቺ የሆነ ጊዜ በየክልሎቹ እንዲወሰን በማድረግ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት /ማስኤ/ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በየክልሉ ተገኝተው አስፈላጊውን ገለጻ አድርገዋል።

በዚህም መሠረት ከአፋርና ከሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በስተቀር በሁሉም ክልሎችና መስተዳድሮች ኮሚሽኖች ከ ታህሳስ 10 እስከ ጥር 4 ቀን 1999 ዓ.ም ባለው ጊዜ ኮሚሽኖቹ እንዲቋቋሙ ተደርጓል። በተመሳሳይ መንገድ ቀደም ሲል የክልል የሕዝብ ቆጠራ በተቋቋመው መልክ ከዞን እስከ ወረዳ ባሉት የአስተዳደር እርከኖች ኮሚሽኖች ተቋቋመው የቆጠራውን ሥራ በማስተባበርና በመከታተል ላይ ይገኛሉ። በከተማና በገጠር ቀበሌዎች የሕዝብ ቆጠራ ኮሚቴዎች የቆጠራው የመስክ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ይቋቋማሉ።

### 3.3.7 <u>የቆጠራውን አጠቃላይ የሥራ ሂደት በሚመለከት</u>

ለቆጠራው የሚደረገው ዝግጅት በአጠቃላይ በኮሚሽኑና በኮሚሽኑ ጽ/ቤት አመራር ልዩ ክትትልና የሥራ ሂደት ግምገማ እየተደረገበት በመከናወን ላይ ያለ ፕሮጀክት ነው። የኮሚሽኑ ጽ/ቤት /የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ/ የአመራር አካላት በሳምንት ሁለት ጊዜ በመደበኛነትና ልዩ ስብሰባዎችንና በየሥራ ክፍሉ በግንባር በመገኘት ያላሰለሰ ክትትል በማድረግ ላይ ይገኛሉ። በዚህም ምክንያት ሥራው በአብዛኛው ከዕቅድ በላይ በተሳካ ሁኔታ በመከናወን ላይ ይገኛል።

## 3.4 <u>ማኅበራዊ ስታቲስቲክስን በተመለከተ</u>

- የኤች. አይ.ቪ/ ኤድስ የባሕሪ ጥናት የመረጃ ማቀነባበር ተግባር ተጠናቆ መረጃው ለተጨማሪ የትንተና ሥራ ለሚመለከተው አካል (ለጤና ጥበቃ ሚ/ር) ተላልፏል። ውጤቱም በአፍሪቃ አዳራሽ የጤና ጥበቃ ሚ/ር እና የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በጋራ ባዘጋጁት አውደጥናት ለሕዝብ ይፋ ሆኖአል።

- በ1998 ዓ.ም የመረጃ መሰብሰብ ተግባር የተካሄደለት የሰው ኃይል ጥናት ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

- ከአሜሪካ መንግስት ጋር በመተባበር የተሠራው የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናት የ(DHS) ውጤት ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል። ውጤቱም በአፍሪቃ አዳራሽ የጤና ጥበቃ ሚ/ር እና የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በጋራ ከመስከረም 28-29 ቀን 1999 ባዘጋጁት አውደ ጥናት ለሕዝብ ይፋ ተደርጓል።

## 4. የ1999 ዓ.ም የዘጠኝ ወራት የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም

በ1999 በጀት ዓመት መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው አዳዲስ ጥናቶችን ለማከናወን በዕቅድ መያዙንና ያከናወናቸውን ሥራዎች በዝርዝር ለማቅረብ ተሞክሯል። የእነዚህን ጥናቶች የፊዚካል አፈፃፀም በተመለከተ ደግሞ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል።

**የ1999 ዓ.ም የፕሮጀክቶች የፊዚካል ሥራ አፈፃፀም**

| ተ.ቁ. | የፕሮጀክት/ የጥናት ዓይነት | ፕሮጀክቱ የሚገኝበት ደረጃ | በ1998 ዓ.ም የተከናወነ | የ1999 ዓ.ም ዕቅድ | የዘጠኝ ወራት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም |
| I | የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም | | | | | | |
| 1 | የግብርና ሰብል ትንበያ ጥናት | አዲስ | 6.75 | 93.25 | 93.25 | 93.25 | 100 |
| 2 | የግብርና ምርት ናሙና ጥናት | | | | | | |
| | - የታረሰ መሬት ስፋትና ምርት መጠን | አዲስ | 6.75 | 93.25 | 93.25 | 80.5 | 86.3 |
| | - የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ | » | 6.75 | 93.25 | 83.25 | 80.3 | 96.4 |
| | - የመሬት አጠቃቀም | » | 6.75 | 93.25 | 83.25 | 80.3 | 96.4 |
| 2.1 | የቤት እንስሳት፣ ዶሮና የንብ ቀፎዎች | » | 6.75 | 93.25 | 93.25 | 93.25 | 100 |
| 2.2 | የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት | » | 6.75 | 93.25 | 74.92 | 50.25 | 67.1 |
| 3. | የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢ.ን.ጥ | » | - | 79.36 | 60.00 | 60.00 | 100 |
| 4. | ወቅታዊ የማምረቻ ድርጅቶች ጥናት | » | 13.00 | 87.0 | 65.75 | 65.75 | 100 |
| 5 | የተፈበረኩ ዕቃዎች የአምራቾች ጥናት | » | 13.00 | 87.0 | 65.75 | 65.75 | 100 |
| 6 | የግብርና ውጤቶች የአም/ ዋጋ ጥናት | » | 9.00 | 91.0 | 67.37 | 67.37 | 100 |
| 7 | የችርቻሮና የአገልግሎት ዋጋ ጥናት | » | 15.00 | 85.0 | 33.27 | 33.27 | 100 |
| II | የሕዝብና ቤት ቆጠራ ፕሮጀክት | | | | | | |
| 1 | የቆጠራ ካርታ ሥራ ማጠናቀቅ | ነባር | 32,458 | 10,000 | 10,000 | 10,451 | 104 |
| 2 | 3ኛው ሕዝብና ቤት ቆጠራ ማካሄድ | አዲስ | - | 65 | 10 | 10 | 100 |

ማሳሰቢያ፡- የቆጠራው ተግባር በ2000 ዓ.ም የሚካሄድለት የአፋር ክልል ካርታ ሥራ በመከናወኑ ከዕቅድ በላይ ለማከናወን ተችሏል።

## 5. የሜቶዶሎጂ ሥራን በተመለከተ

በዚህ የሥራ ክፍል መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው የተለያዩ ጥናቶች የሚያገለግሉ የአሠራር ዘዴዎች ለጥናት የሚያገለግሉ መጠይቆች ጥራት ወካይነታቸውን የማረጋገጥና ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሥራዎች ያከናውናል:: በዚሁ መሠረት በ1999 የዘጠኝ ወራት የሚከተሉት ተግበራት ተከናውነዋል::

### 5.1 ሳምፕሊንግ ሜቶዶሎጂ

- ለ1998 ዓ.ም የምግብ ዋስትና ጥናት የኮድ ቡክ ዝግጅት፣ የ1998 የዋናው መኸርና የበልግ ወቅት የግብርና ጥናት እንዲሁም የተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት የሜቶዶሎጂ ሪፖርት፣ ተጠናቆ ለሚመለከተው ክፍል እንዲተላለፍ ተደርጓል::

- የ1998 የበልግ ወቅት የግብርና ጥናት የተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት weight እና Rate ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል ተላልፏል::

- ለ1999 ዓ.ም. ግብርና ናሙና ጥናት አዲስ ለተከፈቱት ተጨማሪ ሦስት ዞኖች እና ነባር ሆነው በአዲሶቹ ምክንያት ለተከፈሉ አምስት ዞኖች አዲስ የቆጠራ ቦታዎች ምርጫ ተከናውኗል::

- ለ1999 ዓ.ም. ግብርና ናሙና ጥናት ኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ የሚያገለግል ኮድ ቡክ ዝግጅት እንዲሁም weight እና Rate የማዘጋጀት ሥራ የተከናወነ ሲሆን፣ የሜቶዶሎጂ ሪፖርቱም ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል እንዲደርስ ተደርጓል::

- የ1999 ዓ.ም የቤት እንስሳት ጥናት የኤዲቲንግ ኮዲንግ ክትትልና የአካባቢ መለያ ኮዶች የእርማት ሥራ የተከናወነ ሲሆን፣ የሁሉም ክልሎች የWeight እና Rate ሥራም ተጠናቆ ለሚመለከተው አካል ተላልፏል:: በተጨማሪም የውጤቱ ግምገማ ተካሄዶ የሜቶዶሎጂ ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከተው ክፍል እንዲደርስ ተደርጓል::

- የሜቶዶሎጂን ሥራ ይበልጥ ለማሻሻል የሚያስችል ሥራ ለማከናወን ልማዳዊ የአሠራር ሂደቶችን የመፈተሽ፣ ችግሮችን የመለየት ሥራና የማሻሻያ ሃሳቦች ተካተው ዝርዝር ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለመ/ቤቱ የበላይ አካላት እንዲቀርብ ተደርጓል::

- የቤተሰብ ገቢና ወጪ ጥናት የግብርና ናሙና ጥናቶችን በሚመለከት የተለያዩ አማካሪዎች ለማማከር ሲመጡ ሊያተኩሩባቸው የሚገባቸውን ነጥቦች ለማስገንዘብ የሚያስችል ቢጋር ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ቀርቧል።

- የ1996/97 ዓ.ም የቤተሰብ ገቢ፣ፍጆታና ወጪ ጥናትን የሚመለከት ለገቢ መረጃ ብቻ የሚያገለግል እና በ1999 ዓ.ም የታረሰ መሬትና የተገኘ ምርት መጠን እንዲሁም የገጠር ኢንቨስትመንት Climate Survey መሰረት በማድረግ የ Weight ና Rate ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ የሜቶዶሎጂ ሪፖርትም ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ተላልፏል።

5.2 ስታንዳርድና መዛግብት አያያዝን በተመለከተ

- አጠቃላይ በስታንዳርድ ደረጃ ሊያገለግል የሚችል ለሁሉም የሥራ ክፍሎች የጋራ ፅንሰ ሃሣብና ፍችዎች በእንግሊዝኛ ተዘጋጅቷል።

- ለክልሎችና ለዞኖች የሚያገለግል የአካባቢ መለያና ተዛማጅ ኮዶች የተዘጋጁ ሲሆን ለICT ሥራ የሚያገለግል የVariable labeling ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።

5.3 ካርቶግራፊን በተመለከተ

- የ576 ወረዳዎች የቆጠራ ካርታዎችና ሌሎች ተዛማጅ ዶክመንቶች ርክክብ የተፈመ ሲሆን፤ 338 ወረዳዎች ዲጂታይዝድ ተደርገዋል። በአስተዳደር ለውጥ ምክንያት በቢሮ ደረጃ የ150 ወረዳዎች የማስተካከል ሥራ ተካሂዷል። እንዲሁም በመስክ በአምስት ዞኖች ስር ለሚገኙ ወረዳዎች የማሻሻያ ሥራ ተካሂዷል።

- ቀደም ሲል የተሠሩ 327 የቆጠራ ቦታ ካርታዎች በተለያዩ ምክንያት ግድፈት ስለታየባቸው በማስተካከል ለ58 ሠራተኞችና ለ13 ተቆጣጣሪዎች መመሪያና መግለጫውን በመስጠት ወደ ሥራ እንዲሠማሩ ተደርጓል።

- ለውጪ ተገልጋዮች የ106 ወረዳዎች ካርታ በሽያጭ ኮፒ ተደርገው ተሸጠዋል።

- ለሁለተኛና ለሦስተኛ ዙር ስልጠናም የሚያገለግሉ 112,202 የቆጠራ ቦታ ካርታዎች ፎቶ ኮፒ ተደርገው ለሥልጠናው ሥራ ተሠራጭተዋል።

- 80,795 የቆጠራ ቦታ ካርታዎችና 16,405 የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታዎች ለቆጠራ ሎጂስቲክስ አዘጋጅ ኮሚቴ ርክክብ ተፈጽሟል።

## 6 የመረጃ ማቀነባበሪያ ሥራን በተመለከተ

### 6.1 የኤዲቲንግ ኮዲንግና ዳታ ኢንትሪ

በ1999 የዕቅድ ዘመን ዘጠኝ ወራት ውስጥ የ1999 ወርሃዊ የዋጋዎች ጥናት፣ የምግብ ዋስትና ጥናት፣ የ1999 የሰብል ትንበያ ጥናት፣ የቤት እንስሳት ጥናት፣ የሰብል ሁኔታ ግምገማ ጥናት፣ የ1999 ከግብርና ውጭ የሥራ መስክ ጥናት በገጠር የመዋዕለ ነዋይ ፍሰት ጥናት፣ የወቅታዊ ማምረቻ ድርጅቶች ጥናት፣ የዋናው መኸር ጥናት የኤዲቲንግ ኮዲንግ የዳታ ኢንትሪና ክሊኒንግ ሥራ ተጠናቋል፡፡ የ1999 የሰብል ትንበያ ጥናትና የቤት እንስሳት ጥናት የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ እንዲሁም የዳታ ኢንትሪና ክሊኒንግ ሥራ መሉ በሙሉ ተጠናቋል፡፡

እንዲሁም በ1998 ዓ.ም የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባራት የተጠናቀቀላቸው የ1997 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት፣ የ1998 የበልግ ጥናት፣ የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት፣ ወቅታዊ የICT ጥናት መጠይቆች፣ ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት፣ የ1998 የህዝብና ቤት የሙከራ ቆጠራ መጠይቆች የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ እንዲሁም የዳታ ኢንትሪና ክሊኒንግ ሥራ ተጠናቋል፡፡

### 6.2 የሠንጠረዥ ዝግጅት

- በ1999 ዓ.ም የሰብል ትንበያ ጥናት፣ የቤት እንስሳት ጥናት እና የ1999 ወርሃዊ የዋጋዎች ጥናት ሠንጠረዦች ተዘጋጅተው ሪፖርቱን ለሚያወጣ ክፍል ተላልፏል፡፡

- በ1997 እና በ1998 የመረጃ ማሰባሰቡ ሥራ የተጠናቀቀላቸው የ1997 ሰው ሃይል ጥናት፣ የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት፣ የትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪ ጥናት፣ የ1998 የመኸር ወቅት የመሬት ስፋትና ምርት መጠን ጥናት፣ የአጠቃላይ እርሻ ሁኔታ ጥናት፣ የመሬት አጠቃቀም ጥናትና የበልግ ወቅት የመሬት ስፋትና ምርት መጠን ጥናት፣ ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት፣ የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናትና የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ወርሃዊ ጥናት፣ ወርሃዊ የዋጋዎች ኢንዴክስ የሠንጠረዥ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡

- በሌላ በኩል መረጃዎችን ለተጠቃሚዎች አመች በሆነ መንገድ ለማዘጋጀት በታቀደው መሠረት የ1997 የሰው ሃይል ጥናት፣ የ1998 መኸር ወቅት የመሬት ስፋትና ምርት መጠን ጥናት፣ አጠቃላይ የእርሻ ሥራ ሁኔታ ጥናት፣ የመሬት አጠቃቀም መረጃ፣ የበልግ ወቅት ጥናት፣ የአምራቾችና የሸማቾች ዋጋ ጥናት፣ የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ

ጥናት፣ ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት እና የቤት እንስሳት ጥናት መረጃ ወደ SPSS Format የመለወጥ ሥራ ተጠናቋል::

- የ1997 የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት expenditure መረጃ ወደ SPPS እና ወደ ASCII ፎርማት የተለወጠ ሲሆን፤ የዚህ ጥናት income መረጃ ለተለያዩ ሪፖርቶች ዝግጅት የማደራጀቱ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል::

## 6.3 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

- ለ1999 የህዝብ ቤት የሙከራ ቆጠራ መጠይቅ Scanning ሥራ ላይ ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር በጋራ የተከናወነ ሲሆን፣ Scan የተደረገውን መረጃ ለቅንብር ሥራ ምቹ ወደ ሆነ ፎርማት ተቀይሯል:: እንዲሁም Scan ተደርጎ የተዘጋጀውን መረጃ ለመጠቀም የተወሰኑ ሪፖርቶችን በማውጣት ለሚመለከተው ተላልፏል::

- ለህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ የስካኒንግ ክፍልን ለማደራጀት የሚያስፈልጉ የዕቃዎች ዓይነትና ዝርዝር በማዘጋጀት ለሚመለከተው እንዲደርስ ተደርጓል::

- ለህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ Scanning እና Scan የተደረገውን መረጃ ወደ ASCIT Format ለመለወጥ የሚረዳ የ Hard ware እና የSoft ware የሙያ ማሻሻያ የስምንት ቀን ሥልጠና ለ16 የኮምፒውተር ባለሙዎች ተሰጥቷል::

- እ.ኤ.አ የ1995 እና 2000 የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት መረጃን ከ2004 ተመሳሳይ ጥናት መረጃ ጋር ለማወዳደር የሚያስችል Expenditure Ouintile ሠንጠረዦች ተዘጋጅተው ለሚመለከታው ተላልፏል::

- የ2000 እና 2005 የDHS ጥናት ሪፖርትን መሠረት በማድረግ የተመረጡ ሠንጠረዦች መረጃን የማዘጋጀትና የEthiinfo Version 2.0 ዳታ ቤዝ የማደራጀቱ ሥራ ተጠናቋል::

# 7. የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን የማሻሻል ሥራን በተመለከተ

- የመ/ቤቱ የICT እና የተዛማጅ ዕቃዎች ዝርዝር መረጃን ያካተተ ዳታ ቤዝ develop ተደርጎ ተጠናቋል:: በዚህም ዳታ ቤዝ እንዲካተቱ የተደረጉት መረጃዎች አጠቃላይ የመ/ቤቱ የሰው ኃይል፣ የእያንዳንዱ ኮምፒውተር ጠቀሚታ፣ ኦፐሬቲንግ ሲስተም፣ የኮምፒውተር

ፕሪንተሮች ሞዴል፣ በኮምፒውተሮች ላይ የተከሰቱ ቫይረሶችና የሚያጠፉት ዶክመንት ዓይነት፣ ባለፉት ወራቶች የተጠገኑ ኮምፒውተሮችና የመሳሰሉትን የሚያጠቃልል ነው።

- 285 ኮምፒውተሮችና 7 ፕሪንተሮች በተለያዩ ምክንያት ብልሽት ስለደረሰባቸው የመ/ቤቱ ባለሙያዎች የብልሽቱን ክብደትና ቅለት በመፈተሽ ተገቢው ጥገናና የማስተካከል ሥራ ተካሂዶ ለሥራ ብቁ እንዲሆኑ ተደርጓል። በተጨማሪ 256 ኮምፒውተሮች 56 ፕሪንተሮች ከመ/ቤቱ ወጭ ባሉ ባለሙያዎች በዘመናዊ መሣሪያ የአቧራ ጠረጋ ሥራ ተካሂዷል። ቀደም ሲል የነበረው ኔት ወርክ ሲስተም በማሻሻል 100 MB የነበረው ባክቦን ስዊች ወደ 1GB speed dell Switch በሙሉ በ CISCO Switch ተቀይረዋል። እንዲሁም አዲስ ኔትወርክ በመጨመር በአንድ VLAN System ብቻ ይስተናገድ የነበረው ሲስተም ወደ 15 VLAN System ከፍ የማደረግ ሥራ በሂደት ላይ ይገኛል።

- በመ/ቤቱ በተለያዩ ወቅት የተካሄዱ ጥናቶች በማዕከላዊ የመረጃ ማዕከል ተከማችተው የተቀመጡ ሲሆን፣ በቀላሉ ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ለማድረግ ከ400 በላይ ሲዲዎች ተዘጋጅተው ለሽያጭ ቀርበዋል።

- የጂኦግራፊክ ኢንፎርሜሽን የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በማካሄድ ዲጂታይዝድ ተደርገው የተጠናቀቁ የወረዳ ካርታዎችን በማዋሃድ ካርታዎችን የማዘጋጀቱ ተግባር ቅድሚያ የተሰጠው ሲሆን፣ በተመሳሳይ በክልል ውስጥ የሚገኙ የዞን ካርታዎችንም በማዋሃድ የክልል ካርታዎችን በተጓዳኝ የማዘጋጀቱ ሥራ በማካሄድ ላይ ይገኛል።

- የ2004 የማህበራዊ ደህንነት ጥናትና "Ethio-info" መረጃዎችን በመጠቀም በክልልና በዞን ደረጃ አትላስ ለማዘጋጀት ተችሏል። እንዲሁም ከመስክ በGPS ተሰብስበው የመጡ መረጃዎችን በመጠቀም የ329 ወረዳዎች Coordinates ወደ ኮምፒውተር የማስገባት ሥራ ተጠናቋል።

- የተቀላጠፈና አስተማማኝ የሆኑ መረጃዎችን ለተጠቃሚዎች ለማዳረስ የትላልቅና መለስተኛ ኢንዱስትሪ ጥናት መሠረት በማድረግ በሠንጠረዥና የኢንትሪ ሪሌሽን እንዲሁም የዲያግራም ዝግጅት ተጠናቆ ዳታ ሞዴል ተዘጋጅቷል።

- የተዘጋጀው ዳታ ቤዝ በመ/ቤቱ ውስጥ ያለውን የኢንዱስትሪ data በመጠቀም ተሞክሮ አበረታች ውጤት በማስገኘቱ የኢንዱስትሪን ጥናት ዳታ ቤዝ የማዘጋጀቱ ሥራ በአጥጋቢ ሁኔታ ተጠናቋል። በሌላ በኩል ጥሬ መረጃዎችንና ሪፖርቶችን ለመጠቀም ጥያቄ ላቀረቡ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ለተመራማሪዎችና ተማሪዎች ተገቢው አገልግሎት ተሰጥቷል።

- መ/ቤቱ ያከናወናቸውን በመከናወን ላይ ያሉትንና ሊያከናውናቸው ያቀዳቸውን ጥናቶች የሚያመለክቱ በሶስትና ስድስት ወር ለሚወጡ ወቅታዊ የዜና መጽሔቶች በድህረ ገጽ ላይ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

- የ2005 የግብርና ናሙና ጥናት፣ የ2004 የትላልቅ ኢንዱስትሪ ጥናት፣ የ2000 የDHS ጥናትና የ2005 የግብርና ቆጠራ መረጃዎች በማዕከላዊ መረጃ ማከማቻ እንዲቀመጡ ከመደረጋቸውም ባሻገር በሲ.ዲ ተዘጋጅተዋል፡፡

- የ2005/2006 የታረሰ መሬትና የምርት መጠን፣ የመሬት አጠቃቀም፣ የ1995/96 የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት፣ የ1999/2000 የሰው ሃይል ጥናት፣ የትላልቅና መካከለኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናትና የ2006 የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አብስትራክት ሥራዎች በ CD duplicate ተደርጓል፡፡

- የ2004/05 የቤት እንስሳትና ከ1995 እስከ 2006 ያለው የግብርና ናሙና ጥናት CD duplicate ተደርጓል፡፡

## 8. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ሥራን በተመለከተ

### 8.1 የሰው ሃይል አስተዳደር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራምን በሚመለከት

| የዘጠኝ ወራት ዕቅድ | ክንውን |
|---|---|
| ለአዲስ ድርጅታዊ መዋቅር የሰው ኃይል የመደልደል ተግባር ሥራን ማዕከል ያደረገ ይሆን ዘንድ መከታተል፤ | በአዲስ ድርጅታዊ መዋቅር በተፈቀደ የሥራ መደቦች ላይ የሥራ ውጤትን ማዕከል ያደረገ የሠራተኞች ምደባን ለማካሄድ በፌደራል ሲቪል ሰርቪስና በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የወጡ መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ የአብዛኛዎቹ ሠራተኞች ከየካቲት 30/1999 በፊት የጥቂቶቹ ደግሞ ከመጋቢት 30/1999 በፊት ተከናውኖ ደብዳቤ ተሠራጭቷል:: |
| የሰው ኃይል መረጃ ከምፒውተራይዝ እንዲሆን መከታተል፤ | የሰው ኃይል መረጃ ሙሉ በሙሉ ኮምፒውተራይዝድ የሆነ ሲሆን፤ በአሁኑ ሰዓት መረጃውን በቀላሉ ለመጠቀም የሚያስችል ሥራ እየተካሄደ ነው:: |
| አስፈላጊ በሆኑ የሥራ መደቦች ላይ የማሻሻያ ሥራዎችን ማከናወን፤ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን የሥራ ዘርዝር /ፎርም 14/ ማዘጋጀት | በመረጃ ማቀነባበሪያ መምሪያና በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ማስተባበሪያ መምሪያ፣ ለመስክ ሥራ ክንውን መምሪያና ለሌሎች ድጋፍ ሰጪ ዘርፎች የምደባ ደረጃ ማሻሻያ ተጨማሪ የሥራ መደቦችና የአደረጃጀት ጥያቄ ለፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ ቀርቦ ለተወሰኑት ምላሽ የተገኘ ሲሆን ለቀሪዎቹ ክትትል እየተደረገ ይገኛል:: |
| የመ/ቤቱ የሥልጠና ፖሊሲ ሲዘጋጅ መከታተል፤ | የመ/ቤቱ ሙሉ ትኩረት በግንቦት ወር 1999 ዓ.ም. በሚካሄደው 3ኛው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ላይ ስለሆነ ሥራው አልተጀመረም:: |
| የ2000 ዓ.ም የሥልጠና ዕቅድን በማዘጋጀት ለውሳኔ ማቅረብ፤ | ለ2000 የትምህርት ዘመን በሀገር ውስጥ 10 በውጭ አገር 8 በጠቅላላው 18 ሠራተኞች በውድድር ተመርጠዋል:: |
| ለበላይ አመራርና ሌሎች ሠራተኞች የደረት ባጅ በተጨማሪ ማዘጋጀት፤ | የደረት ባጂ ካላቸው ሰራተኞች በተጨማሪ ለሁሉም ሰራተኞች እንዲሰራላቸው የታሰበ ቢሆንም በአዲስ ድርጅታዊ መዋቅር የሰው ኃይል ምደባ የተጠናቀቀው በመጋቢት ወር ላይ በመሆኑ የደረት ባጅ የማዘጋጀቱ ተግባር አልተጀመረም፤ |

### 8.2 የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራምን በሚመለከት

| የዘጠኝ ወራት ዕቅድ | ክንውን |
|---|---|
| መሥሪያ ቤቱ ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ማግኘት የሚፈጀውን ጊዜ፣ በምን ልክ መውሰድ እንደሚቻል እና ሚጠየቅ የክፍያ መጠን /የሚጠየቅ ሆነ/ በመጽሔትና በበሮሸር ነውጣት፤ | የአገልግሎት አይነቶችንና የክፍያ መጠን በማሰባሰብ ሥራ ተጠናቋል:: በተጨማሪም እያንዳንዱን አገልግሎት ለመስጠት የተገመተውን ጊዜ በሙከራ ለማረጋገጥ መረጃው እየተያዘ ነው:: |

8.4 <u>የወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራምን በሚመለከት</u>

| የዘጠኝ ወራት ዕቅድ | ክንውን |
|---|---|
| የዋናው መ/ቤትና የቅ/ጽ/ቤቶች የፋይናንስ እንቅስቃሴ የሚመራበት ማንዋል ሲዘጋጅ መከታተል፤ | በሂሳብ መዝጋት ረገድ የነበረውን መዘግየት ለማጥበብ ያልተወራረዱ ሰነዶች ዕልባት እንዲያገኙ ሥራዎች እየተከናወኑ በመሆኑ ማንዋል የማዘጋጀት ሥራን መጀመር አልተቻለም፤ |
| የዋናው መ/ቤትና የቅ/ጽ/ቤቶች የውስጥ ኦዲት የሚመራበት ማንዋል ሲዘጋጅ መከታተል፤ | በሂሳብ መዝጋት ረገድ የነበረውን መዘግየት ለማጥበብ የውስጥ ኦዲት ሥራዎችን አቅጣጫ የማስያዝ ሥራ እየተከናወነ በመሆኑ ማንዋል የማዘጋጀት ሥራን መጀመር አልተቻለም፤ |
| ለረጅም ጊዜ በሰነድ ተይዘው የሚገኙ ሂሳቦች እልባት እንዲያገኙ መከታተል፤ | በተለይ በቅ/ጽ/ቤቶች ሳይወራረዱ ለረጅም ጊዜ ተንጠልጥለው የሚገኙ ሰነዶች ምክንያቶታቸው እየተጣራ በአብዛኛው መፍትሄ አግኝቷል፤ |

8.5 <u>የሥነ ምግባር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራምን በሚመለከት</u>

| የዘጠኝ ወራት ዕቅድ | ክንውን |
|---|---|
| ሥነ-ምግባር መርሆች ለእይታ አመቺ በሆኑ ቦታዎች ላይ መሰቀሉን መከታተል፤ | የስነ-ምግባር መርሆችን ጽሁፍ እና በፕላስቲክ የመለበድ ሥራ ተጠናቆ ጽሁፉን በፍሬም መስተዋት ውስጥ ለማስቀመጥ በማስፈለጉ እየተሠራ ይገኛል:: |
| የተለያዩ ጥቆማዎችን በመቀበል ለማኔጅሜንት የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ፤ | በሦስት የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች የመንግሥት ተሽከርካሪ አጠቃቀም፣ በገንዘብ አወጣጥ፣ በአድሎአዊ አሠራር፣ ...ወዘተ ላይ የቀረቡ ጥቆማዎችን በማጣራት የውሳኔ ሃሳብ ለዋና ዳይሬክተር ቀርቧል:: ዋና ዳይሬክተርም አብዛኞቹን ጉዳዮች ለዲስፕሊን ኮሚቴ እየቀረቡ ውሳኔ እንዲያገኙ አድርገዋል:: |
| የሃገራችን የሥነ-ምግባር እሴቶችን በመ/ቤቱ መጽሔት ላይ ማውጣት፤ | በመ/ቤቱ መጽሔት ላይ ለማውጣት ዝግጅት በመደረግ ላይ ይገኛል፤ |
| መሠረታዊ የሥነ ምግባር መርሆዎችና አፈፃፀም ላይ ለዋናውና ለቅ/ጽ/ቤት ሠራተኞች ትምህርታዊ ስልጠና መስጠት፤ | በስነ ምግባር መርሆዎች ላይ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ የነበረ ቢሆንም እየተከናወነ ባለው የቆጠራ ዝግጅት ሥራ ማካሄድ አልተቻለም፤ ሆኖም መርሆዎቹ ከማብራሪያ ጋር በመ/ቤቱ መጽሔት ላይ እንዲወጣ ተደርጓል፤ |
| የተለያዩ ኢስነ-ምግባራዊ ድርጊቶችን ማስወገድ የሚያስችሉ ጥናቶችን ማካሄድ፤ | ጥናቶችን ለማካሄድ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በዚህ ዓመት መ/ቤቱ በርካታ የዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥዎች እያከናወነ በመሆኑ በዚህ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መከታተል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ጥናቶችን ማካሄድ አልተቻለም፤ |

| የዘጠኝ ወራት ዕቅድ | ክንውን |
|---|---|
| የሥነ-ምግባር ደንብ ዝግጅት መጠናቀቅን መታተል፤ | በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀውን የሥነ ምግባር ደንብ ለማጠናቀቅ የሌሎች መ/ቤቶችን ተሞክሮ ለማገናዘብ ጥረት የተደረገ ሲሆን፤ አዲስ የወጣው የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 62 ላይ የመንግስት ሠራተኞች የሚተዳደሩበት ዝርዝር የሥነ-ምግባር ደንብ ከዚህ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ለጊዜው ሥራው ተቋርጧል፤ |

## 8.6 ሌሎች በዕቅድ ሳይያዙ የተከናወኑ ሥራዎች

- የኤጀንሲው መ/ቤት የፋይናንስና የኦዲት መምሪያ የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ስለሌሏቸው በባለሙያዎች ለማስያችዝ ማስታወቂያ ወጥቶ በተሰጠው ፈተና ብልጫ ያገኙት ባለሙያዎች ሥራ ጀምረዋል::

- በሌላ በኩል በመ/ቤቱ ፋይናንስ በማንቀሳቀስ፣ በማወራረድና ሪፖርት በማዘጋጀት ረገድ በሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና የማኔጅመንት አባላት በተገኙበት በየሳምንቱ አንድ ቀን በመወያየት እያሉ ችግሮችን ለመፍታት ተችሏል::

- መሥሪያ ቤቱ ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመትና ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት በማቅረብ ረገድ ሲያጋጥሙት የነበሩ ችግሮችን ለመፍታት ያልተማከለ የሂሳብ አሠራር ስርዓት በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ለመተግበር ወስኗል:: የማሻሻያ ስርዓቱም በመጀመሪያ በሰባት ቅ/ጽ/ቤቶች ከጥር 1/1999 ጀምሮ ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን በሌሎቹ 18 ቅ/ጽ/ቤቶች ደግሞ ከሐምሌ 1/1999 ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል:: ለሥራው ውጤታማ መሆንም ለ25ቱም ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ለ18 የአስተዳደርና ሂሳብ ኃላፊዎች የ 2 ቀናት፣ ለሁሉም ኦዲተሮች፣ ሂሳብ ሠራተኞች እና ለ 7 የአስተዳደርና ሂሳብ ሠራተኞች የ9 ቀናት የአቅም ማሳደጊያ ሥልጠና ተሰጥቷል::

- የቅ/ጽ/ቤቶች የሥልጣን ውክልናን ደረጃ በደረጃ ለማሣደግ እየተደረገ ባለው እንቅስቃሴ የኮንትራት ሠራተኞች ቅጥርና ስንብት አፈፃፀምን ወደ ዋናው መ/ቤት በመላክ የይሁንታ መልስ መጠበቅ ሳያስፈልግ በራሣቸው እንዲያጠናቅቁ ውክልና ተሰጥቷል::

- 13 የሚሆኑ የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መሥጠት የማይችሉ በመሆኑ በመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት እንዲወገድ ለበላይ አካል በቀረበው ጥያቄ መሠረት በጨረታ እንዲወገዱ በመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ግምታቸው እየወጣ ይገኛል::

- የሥነ ምግባር መርሆዎችን የመ/ቤቱ ተገልጋዮች እንዲያውቁት ለማድረግ በልሳነ ማ.ስ.ኤ እንዲወጡ ተደርገዋል:: በቀጣይም በላሜራ ላይ ተጽፈው ተገልጋዩ እንዲመለከታቸው ለማድረግ የጽሁፍ ሥራው በመከናወን ላይ ነው::

- በዋናው መ/ቤት ከሚገኙ የሃሳብ መስጫ ሳጥኖች አስተያየት እየተሰበሰቡ ይገኛሉ፤ እንዲሁም በግንቦት ወር 1999 ዓ.ም ላይ ለሚካሄደው ሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ምክንያት በርካታ የዕቃዎች ግዢ እየተከናወነ በመሆኑ የመንግስት ገንዘብ ከብክነት ለመከላከል ክትትል እየተደረገ ይገኛል::

## 9. <u>የሕዝብ ግንኙነት፣ መረጃ ሥርጭትና ትምህርት ሥራን በተመለከተ</u>

| የዘጠኝ ወራት ዕቅድ | ክንውን |
|---|---|
| ልሣነ መስኤን ማዘጋጀትና ማሰራጨት፣ | የመ/ቤቱ ልሳን የሆነው ልሳነ ማስኤ ቅጽ 07 ቁጥር 07 እና ቁጥር 08 መጽሄት እያንዳንዳቸው በ2,000 ኮፒ ታትመው ከመ/ቤቱ ጋር ግንኙነት ላላቸው አካላት ተሰራጭቷል:: |
| ዜና ማስኤን መጽሔት ማዘጋጀትና ማሰራጨት፣ | የመ/ቤቱ ዜና መጽሄት ማስኤ ቅጽ 05 ቁጥር 01 መጽሔት 1,500 ኮፒ ታትሞ ተሠራጭቷል:: |
| የ1999 መልካም ምኞት መግለጫዎችን ማዘጋጀት፣ ማሳተምና ማሰራጨት፣ | 5,000 የግድግዳ የቀን መቁጠሪያዎች እንዲሁም 10,000 ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው የኪስ የቀን መቁጠሪያዎች ታትመው ተሰራጭተዋል:: |
| የመ/ቤቱን ጥናቶች አስመልክቶ በመገናኛ ብዙኃን መግለጫዎችን መስጠት፣ | የመ/ቤቱን የ1999 የሕዝብና ቤት ቆጠራና የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ፣ የህዝብና ቤት ቆጠራን መረጃ በስካኒንግ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም እንዲቻል የተካሄደውን ሥልጠና፣ የ1999 የግብርና ናሙና ጥናት፣ የ1998 የበልግ ወቅት ሰብል ምርት ጥናት ውጤት፣ በከተሞች የሥራ ስምሪት ሁኔታ ጥናት፣ የ1999 የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት፣ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሄት ዝግጅት፣ የአፍሪካ ስታቲስቲክስ ቀንና በሕዝብና ቤት ቆጠራ ስለሚሠማሩ መምህራን ሥልጠናን በተመለከተ ጋዜጣዊ መግለጫ ተሰጥቷል:: ይህንኑ መሠረት በማድረግ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዝንና በጋዜጦች በሥራ ኃላፊዎች የተሰጡ መግለጫዎች የዜና ሽፋን እንዲያገኙና ለህብተሰቡ ግንዛቤን ለማስጨበጥ ጥረት ተደርጓል:: |

| የዘጠኝ ወራት ዕቅድ | ክንውን |
|---|---|
| በመ/ቤቱ የተዘጋጅ የጥናት ሪፖርቶችን በሽያጭ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣ | 2,530 ልዩ ልዩ የጥናት ሪፖርቶች በመጽሐፍ ታትመው በብር 56,837፣ 455 ልዩ ልዩ የጥናት ሪፖርቶች በሲ.ዲ. (CD) ተዘጋጅተው በብር 12,294 እንዲሁም የልዩ ልዩ ጥናቶች ጥሬ መረጃ በብር 37,750 ተሸጧል:: ይህም በበጀት ዓመቱ ኤጀንሲው በሽያጭ ሊያቀርብ ካቀደው ብር 50,000 ጋር ሲነፃፀር 213.7 በመቶውን አከናውኗል:: ክንውኑ ከአጠቃላይ ዕቅዱ ሊበልጥ የቻለው የመረጃ ፈላጊዎች ቁጥር ከዚህ ቀደም ከነበረው እየጨመረ መሆኑና ድጋሚ ሕትመት በመደረጉ እንዲሁም በጥሬ መረጃ ሽያጩም ከታቀደው በላይ መከናወኑ ነው:: |
| በመ/ቤቱ የተዘጋጅ የጥናት ሪፖርቶችን በነጻ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣ | በመ/ቤቱ የተዘጋጁና ግምታቸው ብር 70,000 የሆነ 6,265 ልዩ ልዩ የጥናት ሪፖርቶች ለመንግሥት፣ ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ለከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና ለምርምር ማዕከሎች በነፃ ተሠራጭተዋል:: |
| ዓመታዊ መጽሔቶችንና መጽሐፎችን ማስመረጥና ማስገዛት፣ | በ1999 የዕቅድ ዘመን መጽሐፍ እንዲገዛላቸው ከመ/ቤቱ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች በሚመጡ ጥያቄዎች መሠረት ተጨማሪ መጻሕፍትን ለመግዛት የፍላጐት መጠየቂያ ቅጽ ለሁሉም የሥራ ክፍሎች ተልኮ ቅጾቹ እንዲሞሉ ተደርጐ በአሁኑ ሰዓት የግዥው ሂደት በመከናወን ላይ ይገኛል:: |
| የመ/ቤቱን ቤተመፃህፍት ለተጠቃሚዎች ክፍት ማድረግና በተጠቃሚዎች የሚቀርቡ አገልግሎቶችን እንዲያከናውን ብቁ ማድረግ፣ | የመ/ቤቱ ቤተመጻህፍት ለመ/ቤቱ ሠራተኞችና ከውጪ ለሚመጡ ተገልጋዮች ያልተቋረጠ የንባብ፣ የትውስትና የመረጃ አቅርቦት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል:: |

- ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ 285 የመ/ቤቱን ሪፖርቶች በመረከብና 65 ልዩ ልዩ የውጭና የአገር ውስጥ ህትመቶችን በስጦታና በልውውጥ በማሰባሰብ ቤተ መጻህፍቱን ለማጠናከር ተሞክሯል::

- በቤተ መጻህፍቱ ውስጥ ለውጭ ተገልጋዮች የፎቶ ኮፒ አገልግሎት በመስጠት ብር 1,765.50 ገቢ ተገኝቷል:: "ኢትዮጵያ" ለተሰኘውና በማስታወቂያ ሚኒስቴር በሚዘጋጀው ዓመታዊ መጽሔት ላይ የሚወጣ የመ/ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴ የሚገልጽ ጽሁፍ ተዘጋጅቶ ለማስታወቂያ ሚኒስቴር ተልኳል::

- ለሶስተኛው የህዝብና ቤት ቆጠራ ለህዝብ ማስተማሪያነት የሚያገለግሉ የትምህርትና ቅስቀሳ መሪ ሰነድ፣ ቡሮሽሮችና በጋዜጣ ላይ የሚወጡ በሬዲዮ የሚነበቡ የትምህርትና የቅስቀሳ ጽሁፎች ተዘጋጅተዋል::

## 10. የኦዲት ሥራን በተመለከተ

| የዘጠኝ ወራት ዕቅድ | ክንውን |
|---|---|
| የ1999 በጀት ዓመት ገቢና ወጪ ሂሣብ ምርመራ ማድረግና ለበላይ አካል ሪፖርት ማቅረብ፣ | የ1999 ዓ.ም ሂሳብ ዝርዝር ምርመራ እየተደረገ ሲሆን፤ በካዝና የሚገኝ ጥሬ ገንዘብና ሰነድ ተቆጥሮ የሂሳብ ሪፖርት ለማቅረብ የመ/ቤቱ ሂሳብ እስኪዘጋ እየተጠበቀ ይገኛል:: |
| | የ1998 የመ/ቤቱን የገንዘብ ቤት ካዝና /ሳጥን/ ሂሳብ ምርመራ ተደርጐ ብር 9350.78 ፈሰስ እንዲሆን በማድረግ ሪፖርቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተላልፏል:: |
| የመ/ቤቱ ገንዘብ ቤት በየወሩ የሂሣብ ምርመራ ማድረግና ሪፖርት ማቅረብ፣ | የሐምሌና የነሐሴ ወር የ1998 ዓ.ም እና የመስከረም ወር 1999 ዓ.ም የመ/ቤቱ የሳጥን /ካዝና/ ሂሣብ ምርመራ ተደርጐ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሪፖርት ቀርቧል:: |
| የአገልግሎቱን የሩብ ዓመት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለበላይ አካል ማቅረብ፤ | የ1999 ዓ.ም የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ሪፖርት የተዘጋጀ ሲሆን፤ የሁለተኛውን ሩብ ዓመት ሪፖርት ለማዘጋጀት የፋይናንስ መምሪያ ሂሣቡን ዘግቶ ሪፖርት እንዳቀረበ የሚከናወን ይሆናል:: |
| በመ/ቤቱ አስፈላጊ የሆኑ ቦታዎች ላይ ድንገተኛ ምርመራ ማካሄድና ሪፖርት ማድረግ፤ | የመጽሔት ስርጭትና ሽያጭ ክፍል በተደጋጋሚ ኦዲት ተደርጎ ለበላይ አካል ሪፖርት በመደረጉና እርምጃም በመውሰዱ በአሁኑ ወቅት ክፍሉ አሠራሩን እያሻሻለ ይገኛል:: |
| የመ/ቤቱን የነዳጅ አጠቃቀም ምርመራ አድርጎ ሪፖርት ማቅረብ፤ | በዋናው መ/ቤት የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች የሄዱበትን የኪሎ ሜትር ንባብና የተጠቀሙትን ነዳጅ መሠረት በማድረግ ምርመራ በማካሄድ ሪፖርት ቀርቧል:: በሪፖርቱ ላይም የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎችና ማኔጅመንት የጋራ ስብሰባ በማድረግ የአፈፃፀም አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል |

- የመ/ቤቱን ሠራተኞች የሰዓት ፈርማ ምርመራ ተደርጐ ሪፖርት ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ቀርቧል::

- ለቅ/ጽ/ቤቶች ኦዲተሮች በኦዲት ማንዋል፣ በሞዴል፣ በቋሚና ጊዜያዊ ፋይሎች ላይ ያተኮረ ሥልጠና ለ9 ቀናት ተሰጥቷል::

- የመ/ቤቱ የዕቃ ግምጃ ቤት ኃላፊ የነበሩት በጡረታ ስለሚገለሉ ያንቀሳቅሱ የነበረውን ንብረት መርመራ ተደርጐ ሪፖርቱ ለበላይ አካል ቀርቧል:: በተጨማሪም የዕቃ ግምጃ ቤት

- ከሐምሌ 1997 ዓ.ም. ጀምሮ የተቋረጠ የበረሃ አበል ይከፈለን በማለት በተለያዩ ፍ/ቤቶች ባቀረቡት ክስ ላይ በዚህ ዘጠኝ ወራት ውስጥ በተደረገው ክትትል ጉዳዩን ሲመለከት የነበረው ፍ/ቤት መ/ቤቱን በነፃ አሰናብቶታል፡፡

- በመ/ቤቱ ላይ የአፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ የመሠረተው የብር 5,649.98 የፍትሐብሔር ክስ በተደረገው ክትትል ፍ/ቤቱ ክሱን በይርጋ ቀሪ በማድረግ መዝገቡን ዘግቶ መ/ቤቱን በነፃ አሰናብቶታል፡፡

## 12. የፕላንና ፕሮግራም ሥራን በተመለከተ

| የዘጠኝ ወራት ዕቅድ | ክንውን |
|---|---|
| የ1999 በጀት ዓመት የካፒታል በጀት ወርሃዊ የፋይናንስ ፍላጐት ማዘጋጀትና ለበላይ አካል ማስተላለፍ፤ | በ1999 በጀት ዓመት መ/ቤት ለሚያካሂዳቸው ሁለት ፕሮጀክት የተመደበውን የካፒታል በጀት ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር በመሆን ወርሃዊ የፋይናንስ ፍላጐት በማዘጋጀት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ |
| የበጀት ዕጥረት በሚታይባቸው የወጪ መደቦችን በመለየትና ዝውውር ማዘጋጀት፤ | መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው ሁለት የካፒታል ፕሮጀክቶች ላይ በተፈቀዱ የተለያዩ ርዕሶች እጥረት የታየባቸውን በመለየት የዝውውር ጥያቄ ለሚመለከተው ክፍል አቅርቦ ዝውውሩ ተፈጽሟል፡፡ |
| የመ/ቤቱን አጠቃላይ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለበላይ አካል ማስተላለፍ፤ | የ1999 ዓ.ም የመጀመሪያና ሩብ ዓመትና የስድስት ወራት ሪፖርትን እንዲሁም የ1998 ዓ.ም ዓመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርትን በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ አድርጓል፡፡ |
| የስታቲስቲክስ ዕቅድና የካፒታል በጀት ፍላጐት ማዘጋጀትና ለበላይ አካል ማስተላለፍ፤ | የ2000 በጀት ዓመት የስታቲስቲክስ ዕቅድና የካፒታል በጀት ፍላጐትን ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ጋር በጋራ በማዘጋጀት ለበላይ አካል አስተላልፏል፤ |

## 13 የሰው ሃብት ሥራ አመራር ሥራን በተመለከተ

### 13.1 የሰው ኃይል

| የዘጠኝ ወራት ዕቅድ | ክንውን |
|---|---|
| ለመዋቅር ድልድል የቋሚ ሠራተኞች ማህደር በማጣራት መረጃዎችን መሰብሰብ፣ | በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች ተቀጥረው የሚሰሩ ሁሉም ቋሚ ሰራተኞች ማህደር የማጣራት ስራ ተከናውኗል፡፡ |
| ለመዋቅር ድልድል የ9 ወር የቋሚ ሠራተኞች ምዘና ውጤት ተከታትሎ መረከብና ማያያዝ፣ | በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች ተቀጥረው የሚሰሩ ሁሉም ቋሚ ሰራተኞች የዘጠኝ ወር ምዘና ስራ ተከናውኗል፡፡ |
| በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች የቋሚ ሠራተኞች አዲስ ቅጥር መፈፀም፣ | የሰላሳ ሁለት ቋሚ ሰራተኞች ቅጥር ተካሂዷል፡፡ |

| የዘጠኝ ወራት ዕቅድ | ክንውን |
|---|---|
| በመ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር መሠረት ሠራተኞች የድልድል ደብዳቤ መስጠት፤ | በመ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር መሠረት በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ ለ1,130 እንዲሁም በዋናው መ/ቤት ለ446 በድምሩ ለ1,576 ሠራተኞች የድልድል ደብዳቤ ተሰጥቷል፤ |
| በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች የኮንትራት ሠራተኞች መቅጠርና ቅጥራቸውን ማቋረጥ፣ | የ2,508 ኮንትራት ሠራተኞች ቅጥር የተፈፀመ ሲሆን በተመሳሳይ የ2,936 ኮንትራት ሠራተኞች ቅጥር ተቋርጧል:: |
| ዓመታዊ የሰው ኃይል አስተዳደር ተግባራትና ማከናወን፣ | የመ/ቤቱን ቋሚና ኮንትራት ሰራተኞች ቅጥር፣ ዝውውር፣ ጡረታ፣ የዓመት ዕረፍት.. ወዘተ ሥራ ተከናውኗል:: |

<u>የሰው ኃይል ሁኔታ</u>

| ተ ቁ | አጠቃላይ ሁኔታ | የሠራተኛ ቅጥር ሁኔታ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ቋሚ | ኮንትራት | ድምር |
| 1 | በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ | 1,662 | 1,326 | 2,988 |
| 2 | አዲስ የተቀጠሩ | 32 | 2,508 | 2,540 |
| 5 | በተለያዩ ምክንያት ሥራ የለቀቁ | (52) | (2,936) | (2,988) |
| 6 | በጡረታ የተገለሉ | (3) | - | (3) |
| 7 | በሞት የተለዩ | (15) | - | (15) |
| 8 | አሁን ያለው የሰው ኃይል | 1,624 | 898 | 2,522 |

**ማስታወሻ፣** ኮንትራት ሠራተኞችን በሚመለከት ሥራ የለቀቁ የሚለው ኮንትራታቸውን ጨርሰው የተሰናበቱ መሆኑ ግልፅ ሊሆን ይገባዋል::

## 14 <u>የፋይናንስ ሥራን በተመለከተ</u>

በ1999 በጀት ዓመት የኤጀንሲው መ/ቤት ለሚያካሂደው ብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ብር 31,104,800.00፣ ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ፕሮጀክት ብር 277,733,000.00 እና ለመደበኛ በጀት ብር 18,318,900.00 በድምሩ ብር 327,156,700.00 ተፈቅዷል::

### ሀ. <u>መደበኛ በጀት</u>

ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው መደበኛ በጀት ውስጥ ለደመወዝ ብር14,911,500 ለሥራ ማስኬጃ ብር 3,407,400 የተመደበ ሲሆን፣ ከሐምሌ 1/1998 ዓ.ም እስከ መጋቢት 30/1999 ዓ.ም ድረስ የመደበኛ ደመወዝና ሥራ ማስኬጃ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቶ ገቢ የሆነው ብር 13,990,930 ሲሆን፤ በሥራ ላይ የዋለው ደግሞ ብር 13,849,478 ነው:: አፈፃፀሙም በእጅ ከገባው ጋር ሲነፃፀር 98.9 % ነው::

ለ. የካፒታል በጀት

የኤጀንሲው መ/ቤት በ1999 ዓ.ም ለሚያካሂደው ብሔራዊ የተቀናጀ ስርቬይ ፕሮግራም ብር 31,104,800.00 የተመደበ ሲሆን ከሐምሌ 1/1998 ዓ.ም እስከ መጋቢት 30/1999 ዓ.ም ድረስ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቶ ገቢ የሆነው ብር 28,526,650 ሲሆን፤ ወጪ የሆነው ደግሞ ብር 23,807,623 ነው፡፡ በዘጠኝ ወራት ውስጥ ገቢ የሆነው ወጪ ከተደረገው ጋር ሲነፃፀር 83.4 በመቶ ሲሆን ለዓመቱ ከተመደበው ጋር ደግሞ 76.5 በመቶ ይሆናል፡፡

እንዲሁም ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ብር 277,733,000 የተመደበ ሲሆን፤ ከሐምሌ 1/1998 ዓ.ም እስከ መጋቢት 30/1999 ዓ.ም ድረስ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቶ ገቢ የሆነው ብር 28,327,068 ሲሆን፤ ወጪ የሆነው ደግሞ ብር 17,834,253 ነው፡፡ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ገቢ የሆነው ወጪ ከተደረገው ጋር ሲነፃፀር 63.0 በመቶ ሲሆን፤ ለዓመቱ ከተመደበው ጋር ሲነፃፀር ደግሞ 6.4 በመቶ ይሆናል፡፡ በዘጠኝ ወራቱ የተከናወነው ከታቀደው አነስተኛ የሆነው ለዚህ ፕሮጀክት የተመደበው በጀት በአብዛኛው ተግባራዊ የሚሆነው ለክልሎች በመጋቢት ወር 1999 ከተሰራጨ በኋላ ነው፡፡ ምክንያቱም ለሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ከተያዘው የካፒታል በጀት ውስጥ ከብር 241 ሚሊዮን ተግባራዊ የሚሆነው በግንቦት ወር በክልሎች በኩል በመሆኑ ነው፡፡ ዝርዝሩም በሚቀጥሉት ሠንጠረዦች ላይ ቀርቧል፡፡

ሐ. <u>ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች</u>

| የዘጠኝ ወራት ዕቅድ | ክንውን |
|---|---|
| በመደበኛ በካፒታል በጀት የወርሃዊ የፋይናንስ ፍላጐት መሠረት በየወሩ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጥያቄ በማቅረብና ለሥራ ማስኬጃ ያን ለደመወዝ የሚከፈል ገንዘብ በማምጣት ክፍያዎችን መፈፀም፣ | በመደበኛና በካፒታል በጀት ወርሃዊ የፋይናንስ ፍላጐትን መሰረት ያደረገ ጥያቄ በማቅረብ ለደመወዝና የስራ ማስኬጃ ክፍያዎች ተፈፅሟል፡፡ |
| በካፒታል በጀት ለሚከናወኑ ሁለት ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ገንዘብ በወቅቱ ለማመለከታቸው የሥራ ክፍሎችና ለቅ/ጽ/ቤቶች በባንክ መላክ፣ ክፍያም እንዲፈፀም ማድረግ፣ | ከመስክ ሥራ ክንውን መምሪያ ለቅ/ጽ/ቤቶች በሚቀርበው ጥያቄ መሰረት ለፕሮጀክቶቹ ማስፈፀሚያ የሚውል ገንዘብ በባንክ እንዲላክ ተደርጓል፡፡ |
| ወርሃዊ ሂሣቦችን በገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተዘጋጁ የኮምፒውተር ሶፍትዌሮች በመጠቀም መመዝገብና ሂሣብ መዘጋት፣ | የ1999 በጀት ዓመት የሰባት ወር የሂሳብ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተልኳል፡፡ |

| የዘጠኝ ወራት ዕቅድ | ክንውን |
|---|---|
| የመ/ቤቱን የ1998 በጀት ዓመት አጠቃላይ ሂሣብ ተፈቅዶ ሥራ ላይ ከዋለው ጋር አጣጥሞ መዝጋት፣ | የ1998 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርት ተጠናቆ ለገንዘ ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ቀርቧል፡፡ በዋናው አዲ ሂሳቡም ተመርምሯል፡፡ |
| የቅ/ጽ/ቤቶችን የሂሣብ ሰነዶች መረከብ፣ መመዝገብና ሂሣባቸውን ወቅታዊ ማድረግ፣ | የቅ/ጽ/ቤቶችን የሂሣብ ሰነዶች በመረከብ፣ በመመዝገ ሂሣባቸውን በመከታተል ሂሳባቸው ወቅታዊ እንዲ ተደርጓል፡፡ |

- በሰባት ቅ/ጽ/ቤቶች ከጥር 1 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ያልተማከለ የሂሳብ አሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ የጥርና የየካቲት ወር ሪፖርትን በአጥጋቢ ሁኔታ ያቀረቡ ሲሆን፤ ይህንን አሰራር በጀመሩ ቅ/ጽ/ቤቶች ተገቢ የሆነ የሙያ እገዛ በማንባር በመገኘት ተሰጥቷል፡፡ ከዚህ በመነሳትም እስከ ሰኔ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ የድርጊት መርሃ ግብር በመንደፍ መሟላት በሚገባቸው የማቴሪያልና የሰው ኃይል እንዲሟላና ላሉትም ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል፡፡

- በ1999 ዓ.ም ተግባራዊ ለተደረገው አዲስ መዋቅር የሚያስፈልገውን ተጨማሪ በጀት አዘጋጅተን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጥያቄ በማቅረብ ክፍያ ተፈጽሟል፡፡

- የ2000 በጀት ዓመት የመደበኛ በጀት ተዘጋጅቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ቀርቧል፡፡

- በየወቅቱ የበጀት ቁጥጥር በማድረግ እጥረት ባጋጠማቸው የበጀት እርዕሶች ላይ የዝውውር ጥያቄ ቀርቦ ተፈጽሟል፡፡

# የመደበኛ በጀት አጠቃቀም

| ተ. ቁ.. | የበጀት አጠቃቀም | ለ1999 ዓ.ም ከመንግሥት ግምጃ ቤት የተፈቀደ | ለመዋቅር ማስተካከያ የተፈቀደ በጀት | የተስተካከለ በጀት | የዘጠኝ ወራት ዕቅድ | ከገንዘብ ሚ/ር ተጠይቆ ገቢ የሆነ | ገቢ ከሆነው ውስጥ በሥራ ላይ የዋለ | አፈፃፀም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | ከታቀደው | ተጠይቆ ከመጣው |
| | 01 | 02 | 03 | 04 | 05 | 06 | 07 | 08 | 09 |
| 1 | **መደበኛ በጀት** | **18,318,900** | **1,803,340** | **20,122,240** | **13,990,930** | **13,990,930** | **13,849,478** | **100** | **98.9** |
| | 6111 | 14,911,500 | 1,701,265 | 16,612,765 | 11,211,300 | 11,211,300 | 11,660,695 | 100 | 104 |
| | 6121 | 90,300 | | 90,300 | 55,800 | 55,800 | 57,659 | 100 | 103 |
| | 6131 | 894,700 | 102,075 | 996,775 | 671,040 | 671,040 | 702,784 | 100 | 105 |
| | 6211 | 195,600 | | 195,600 | 195,600 | 195,600 | 175,007 | 100 | 89 |
| | 6212 | 200,000 | | 200,000 | 200,000 | 200,000 | 80,161 | 100 | 40 |
| | 6217 | 157,300 | | 157,300 | 117,990 | 117,990 | 101,001 | 100 | 86 |
| | 6218 | 43,000 | | 43,000 | 43,000 | 43,000 | 10,167 | 100 | 24 |
| | 6219 | 10,000 | | 10,000 | 10,000 | 10,000 | - | 100 | 0 |
| | 6231 | 15,000 | | 15,000 | 12,000 | 12,000 | 2,952 | 100 | 25 |
| | 6232 | 10,000 | | 10,000 | 8,000 | 8,000 | 1,286 | 100 | 16 |
| | 6233 | 18,200 | | 18,200 | 13,680 | 13,680 | 6,508 | 100 | 47 |
| | 6241 | 111,000 | | 111,000 | 111,000 | 111,000 | 82,902 | 100 | 75 |
| | 6243 | 80,000 | | 80,000 | 80,000 | 80,000 | 33,703 | 100 | 42 |
| | 6244 | 20,000 | | 20,000 | 20,000 | 20,000 | 15,538 | 100 | 78 |
| | 6252 | 584,400 | | 584,400 | 438,300 | 438,300 | 438,280 | 100 | 99 |
| | 6253 | 50,000 | | 50,000 | 40,000 | 40,000 | 14,063 | 100 | 35 |
| | 6254 | 6,000 | | 6,000 | 6,000 | 6,000 | 675 | 100 | 11 |
| | 6255 | 12,000 | | 12,000 | 9,600 | 9,600 | 2,390 | 100 | 25 |
| | 6256 | 52,400 | | 52,400 | 39,330 | 39,330 | 18,031 | 100 | 46 |
| | 6257 | 124,000 | | 124,000 | 93,060 | 93,060 | 72,852 | 100 | 78 |
| | 6258 | 439,600 | | 439,600 | 329,760 | 329,760 | 192,838 | 100 | 58 |
| | 6259 | 339,000 | | 33,900 | 25,470 | 25,470 | 18,741 | 100 | 73 |
| | 6271 | 10,000 | | 10,000 | 10,000 | 10,000 | 100 | 100 | 1 |
| | 6314 | 250,000 | | 250,000 | 250,000 | 250,000 | 161,143 | 100 | 64 |

## የተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም
## የዘጠኝ ወራት የፋይናንስ አጠቃቀም መግለጫ

| የሂሳብ መደብ | ጠቅላላ የተፈቀደ | የተዛወረ | | የተስተካከለ በጀት | ለዘጠኝ ወራት የታቀደ | ከገ/ሚ/ር ተጠይቆ የመጣ | እስከ መጋቢት ወጪ የሆነ | አፈፃፀም በመቶኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በመጨመር | በመቀነስ | | | | | ከታቀደው | ተጠይቆ ከመጣው |
| 01 | 02 | 03 | 04 | 05 | 06 | 07 | 8 | 09 | 10 |
| 6113 | 12,789,500 | | 2,236,000 | 10,553,500 | 9,798,700 | 9,440,500 | 7,685,733 | 78 | 81 |
| 6114 | 3,123,200 | | 520,000 | 2,603,200 | 2,543,200 | 2,307,400 | 1,706,095 | 67 | 74 |
| 6123 | 880,900 | | | 880,900 | 871,900 | 773,200 | 487,805 | 56 | 63 |
| 6211 | 400,000 | | | 400,000 | 400,000 | 400,000 | 68,845 | 17 | 17 |
| 6212 | 420,000 | | | 420,000 | 390,000 | 370,000 | 162,663 | 42 | 44 |
| 6213 | 300,000 | | | 300,000 | 300,000 | 300,000 | 31,784 | 11 | 11 |
| 6217 | 2,300,000 | | | 2,300,000 | 1,918,500 | 1,947,800 | 1,921,686 | 100 | 99 |
| 6231 | 3,500,000 | 1,500,000 | | 5,000,000 | 4,830,200 | 5,000,000 | 4,823,155 | 100 | 96 |
| 6232 | 209,500 | 300,000 | | 509,500 | 509,500 | 424,700 | 388,694 | 76 | 92 |
| 6241 | 2,800,000 | | | 2,800,000 | 2,746,800 | 2,713,000 | 2,296,260 | 84 | 85 |
| 6243 | 100,000 | | | 100,000 | 80,000 | 41,000 | 2,036 | 3 | 5 |
| 6252 | 652,600 | 60,000 | | 712,600 | 671,800 | 560,700 | 452,863 | 67 | 81 |
| 6254 | 1,090,100 | | | 1,090,100 | 1,090,100 | 1,090,100 | 920,456 | 84 | 84 |
| 6255 | 85,000 | | | 85,000 | 74,000 | 85,000 | 32,650 | 44 | 38 |
| 6256 | 50,000 | | | 50,000 | 40,000 | 40,000 | 20,142 | 50 | 50 |
| 6257 | 44,000 | 20,000 | | 64,000 | 51,500 | 44,500 | 38,969 | 76 | 88 |
| 6258 | 400,000 | | | 400,000 | 325,000 | 235,000 | 180,841 | 56 | 77 |
| 6259 | 60,000 | 20,000 | | 80,000 | 65,000 | 53,000 | 54,749 | 84 | 103 |
| 6271 | 1,900,000 | 856,000 | | 2,756,000 | 2,756,000 | 2,700,750 | 2,532,197 | 92 | 94 |
| ድምር | **31,104,800** | **2,756,000** | **2,756,000** | **31,104,800** | **29,462,200** | **28,526,650** | **23,807,623** | **81** | **83** |

# የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ፕሮጀክት
## የዘጠኝ ወራት የፋይናንስ አጠቃቀም መግለጫ

| የሂሳብ መደብ | ጠቅላላ የተፈቀደ | የተዛወረ | | የተስተካከለ በጀት | እስከ መጋቢት የታቀደ | ለክልል ኮሚሽን የተላከ | በኤጀንሲው ጥቅም ላይ የሚውል | ከገ/ሚ/ር ተጠይቆ የመጣ | በኤጀንሲው እስከ መጋቢት ወጪ የሆነ | በጀት አጠቃቀም በመቶኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በመጨመር | በመቀነስ | | | | | | | ከታቀደው | ተጠይቆ ከመጣው |
| 01 | 02 | 03 | 04 | 05 | 06 | 07 | (06-07)=08 | 09 | 10 | 11 | 13 |
| 6113 | 6,978,900 | | 2,900,000 | 4,078,900 | 2,736,030 | 0 | 2,736,030 | 3,842,205 | 2,525,037 | 92 | 66 |
| 6114 | 8,594,900 | 50,000 | 2,587,735 | 6,057,165 | 6,007,165 | 4,962,340 | 1,044,825 | 1,044,825 | 670,040 | 11 | 64 |
| 6116 | 0 | 996,600 | | 996,600 | 0 | 996,600 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 6123 | 383,700 | | 109,010 | 274,690 | 193,110 | 0 | 193,110 | 274,420 | 101,387 | 53 | 37 |
| 6212 | 2,607,300 | 94,100 | | 2,701,400 | 2,662,900 | 140,600 | 2,522,300 | 2,559,800 | 273,459 | 10 | 11 |
| 6213 | 3,900.800 | | 2,245,460 | 1,655,340 | 1,655,340 | 0 | 1,655,340 | 1,655,340 | 4,319 | 0 | 0 |
| 6217 | 7,800,000 | 100,000 | 1,500,000 | 6,400,000 | 5,950,860 | 4,546,800 | 1,404,060 | 1,490,474 | 1,348,393 | 23 | 90 |
| 6218 | 262,000 | | | 262,000 | 262,000 | 0 | 262,000 | 262,000 | 64,183 | 24 | 24 |
| 6231 | 114,000.000 | 8,605,640 | 200,000 | 122,405,640 | 122,156,840 | 115,843,862 | 6,312,978 | 5,389,896 | 4,868,248 | 4 | 90 |
| 6232 | 387,000 | 3,623,142 | | 4,010,142 | 3,999,142 | 3,833,100 | 166,042 | 131,800 | 97,851 | 2 | 74 |
| 6233 | 0 | 54,000 | | 54,000 | 0 | 0 | 0 | 0 | 14,899 | 0 | 0 |
| 6241 | 4,200,000 | | | 4,200,000 | 3,578,840 | 114,000 | 3,464,840 | 3,172,502 | 2,936,400 | 82 | 93 |
| 6243 | 825,500 | | 600,000 | 225,500 | 169,850 | 0 | 169,850 | 209,000 | 4,336 | 3 | 2 |
| 6251 | 1,850,000 | | 171,000 | 1,679,000 | 1,850,000 | 109,700 | 1,740,300 | 1,540,000 | 37,085 | 2 | 2 |
| 6252 | 448,500 | | 448,500 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 6253 | 66,000 | | | 66,000 | 66,000 | 0 | 66,000 | 66,000 | 44,753 | 68 | 68 |
| 6254 | 3,500,000 | | | 3,500,000 | 3,500,000 | 0 | 3,500,000 | 598,000 | 320,431 | 9 | 54 |
| 6255 | 439,200 | 1,005,820 | | 1,445,020 | 1,245,020 | 664,320 | 580,700 | 439,200 | 6,600 | 1 | 2 |
| 6256 | 254,700 | 226,828 | | 481,528 | 452,528 | 74,600 | 377,928 | 89,600 | 18,112 | 4 | 20 |
| 6257 | 34,500 | | | 34,500 | 34,500 | 0 | 34,500 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 6258 | 1,200,000 | | 600,000 | 600,000 | 523,200 | 437,350 | 85,850 | 157,640 | 81,361 | 16 | 52 |
| 6259 | 0 | 20,000 | | 20,000 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 6271 | 95,000,000 | 24,186,000 | 3,414,425 | 115,771,575 | 115,281,635 | 109,964,623 | 5,317,012 | 4,590,818 | 4,264,611 | 4 | 93 |
| 6311 | 0 | 600,000 | | 600,000 | 600,000 | 0 | 600,000 | 600,000 | 0 | 0 | 0 |
| 6313 | 25,000,000 | | 24,786,000 | 214,000 | 214,000 | 0 | 214,000 | 213,548 | 160,346 | 75 | 75 |
| ድምር | **277,733,000** | **39,562,130** | **39,562,130** | **277,733,000** | **273,138,960** | **241,687,895** | **31,451,065** | **28,327,068** | **17,841,851** | **7** | **63** |

ማሳሰቢያ፦ አብዛኛው የቆጠራ ማስፈፀሚያ በጀት ሥራ ላይ የሚውለው ከሚያዝያ ወር 1999 ዓ.ም በኋላ ሲሆን፣ ገንዘቡን ቀደም ብሎ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለመጠየቅ የተፈለገው ወደክልሎች ቶሎ ደርሶ ጥቅም ላይ በወቅቱ እንዲደርስ በማስፈለጉ ነው። በዚህም ምክንያት በበጀት አፈፃፀሙ ላይ ዝቅተኛ የሆነ ውጤት ታይቷል።

## 15 የቴክኒክና ንብረት አስተዳደርን ሥራ በተመለከተ

| የዘጠኝ ወራት ዕቅድ | ክንውን |
|---|---|
| የ1999 ዓመታዊ የደንብ ልብስ ግዥ ማከናወን፣ | በዋናው መ/ቤትና በስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች የደንብ ልብስ የሚያስፈልጋቸውን የሠራተኞች ቁጥር በማጣራት ጨረታው በጋዜጣ እንዲወጣ ተደርጎ፣ ጨረታውም አሸናፊው ተለይቶ እና ግዥው ተፈፅሞ ለተጠቃሚዎች በመሠራጭት ላይ ይገኛል:: |
| የ1999 ዓመታዊ የጽ/መሣሪያ፣ የሕትመትና ቋሚ ዕቃዎችና ሌሎች ግዥዎችን ማከናወን፣ | የጫማ፣ የጎማ፣ የኮምፒውተር፣ የጽሕፈት መሳሪያ፣ ካርቶን ግዥ፣ እንዲሁም የጠረጴዛ፣ ወንበርና መደርደሪያ ለመግዛት የጨረታ ዶኩመንት ተሸጦ አሸናፊው ተለይቶ ግዥውን በመፈጸም ዕቃዎቹ ገቢ ተደርገው ሥራ ላይ ውለዋል:: |
| ወርሃዊ የስልክ፣ የመብራት፣ የውሃና ሌሎች ክፍያዎችን መፈፀም፣ | የቤት ኪራይ፣ የውሃ፣ የመብራት ፍጆታን ቢሉን በመመልከትና በማጣራት ክፍያው ተፈጽሟል:: |
| የኮምፒውተር፣ የፕሪንተር፣ የሂሳብ መኪናዎችና ሌሎች የማተሚያ መሣሪያዎችን ማስጠገን፣ | የኮምፒውተር ፕሪንተር ጥገናና ሑሣ ግዥ ለመፈጸም የጨረታ አሸናፊው ተለይቶ በአሁኑ ሰዓት የጥገና ሥራው በመካሄድ ላይ ይገኛል:: |
| የመ/ቤቱን ተሽከርካሪ በደንበኞች ጋራዥ ማስጠገንና እየተከታተሉ ማውጣት፣ | በሞኢንኮ 98፣ በኒያላ ሞተርስ 57፣ በኢትዮ ሌክስ 115፣ ዓባይ ቴክኒክ 55፣ ጀነራል ሞተርስ 69፣ በደግነት ጉተማ ጋራዝ 12 እና በኢትዮ ኢንቨስትመንት ጋራዥ 12 ተሽከርካሪዎች ለጥገና ገብተው እንደቅደም ተከታላቸው ከሞኢንኮ 96 ከዓባይ ቴክኒክ 33፣ ከጀነራል ሞተርስ 60፣ ከደግነት ጉተማ ጋራዥ 11 እንዲሁም ከኢትዮ ኢንቨስትመንት ጋራዥ 12 ተሽከርካሪዎች ጥገናቸው ተጠናቆ ለአገልግሎት ተሰማርተዋል:: ከዚህ በተጨማሪም በመ/ቤቱ ጋራዥ 105 ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት ሰጥተዋል:: (አንድ ተሽከርካሪ ከሁለት ጊዜ በላይ ተጠግኗል) |
| ዓመታዊ የኢንሹራንስና የተመረጡ የጥናት ጋራዦችና ማዕከላት ጋር ውል ማደስ፣ | ከተጠቀሱት ድርጅቶች ጋር አስፈላጊው ዓመታዊ ውል ታድሶ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል:: |
| ዓመታዊ የቋሚና አላቂ ዕቃዎች የደንብ ልብስና ሌሎች ዕቃዎችን ስርጭት ማካሄድ፣ | በበጀት ዓመቱ የተገዙና ካለፈው ዓመት የተላለፉ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች ለቅ/ጽ/ቤቶችና ለዋናው መ/ቤት ለሥራ ሲጠይቁ ሥርጭት እየተደረገ ይገኛል:: |

- ለመ/ቤቱ የአትላስ ሕትመት ሥራ በጨረታ ወጥቶ ከአሸናፊውን ድርጅት ጋር ውለታ በመዋዋል ሥራው በመካሄድ ላይ ይገኛል።

- የመ/ቤቱን ሥራ በተገቢው መንገድ ለማካሄድና ለማፋጠን የቢሮ ዝውውርና የሽግሽግ ሥራና የቀድሞው የህዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ንብረት ወደዋናው መ/ቤት የማዛወርና የማሽጋሸግ ሥራ በመሥራትና ለቆጠራው ሥራ የሚያገለግሉ ጊዜያዊ መጠለያዎችንም ጭምር በማዘጋጀት ለሥራ ብቁ ሆነዋል።

- ከሐምሌ 1/1998 ጀምሮ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ተካሄዶ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ ሪፖርቱ ተዘጋጅቷል።

- ከሐምሌ 1/1997 እስከ ሰኔ 30/1998 ድረስ ለተለያዩ ቅ/ጽ/ቤቶች የተላኩ ልዩ ልዩ ዕቃዎች ለመድረሳቸው ዝርዝሩ ለ25 ቅ/ጽ/ቤቶች ተሠራጭቶ መረጃዎች ተሰብስበው በመመርመር ላይ ይገኛል።

- ለመ/ቤቱ አገልግሎት ለሚውሉ የተለያዩ ዕቃዎች ማከማቻ ለሚሠራው መጋዘን በወጣው ጨረታ መሠረት በአሸናፊው ኮንትራክተር በተለይ ለስንኒንግ ሥራ የሚያገለግለው የመጋዘን ግንባታ ተጠናቆ አገልግሎት ላይ ውሏል።

- መ/ቤቱ ሲጠቀምባቸው የኖሩና አሁን ግን ከአገልግሎት ውጭ የሆኑትና የሚወገዱ ዕቃዎችን ለማስወገድ በዋጋ ገማችና በአስወጋጅ ኮሚቴ በጋራ በተደረሰው ስምምነት መሠረት የተወሰኑ ዕቃዎች ሲወገዱ የተወሰኑት በውሳኔው መሠረት ተግባራዊ ለማድረግ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተጠናቀዋል።

## 15.1 ትራንስፖርትና ጥገና

- ለመ/ቤቱ አገልግሎት የሚሰጡ የሁሉም ተሽከርካሪዎች የቅድመ ምርመራ ሥራ ተካሄዶ በዋናው መ/ቤትና ከቅ/ጽ/ቤቶች ለሥራ በመጡ ተሽከርካሪዎች ምርመራ ተደርጓል። እንዲሁም 23 የሚሸጡ ተሽከርካሪዎች የቅድመ ሁኔታዎች ሥራዎች ተጠናቆ ለሽያጭ በመንገድ ትራንስፖርት መ/ቤት በቀጠሮ ላይ ይገኛሉ።

- የሁለት ሞተር ሳይክሎችና የ50 ስቴሽን ዋገን የመስክ ተሽከርካሪዎች ሊብሬና ታርጋ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

- በሌላ በኩል በዚህ ዘጠኝ ወራት ውስጥ 20,419 ሊትር ቤንዚን፣ 24,387 ሊትር ናፍታ፣ 685 ሊትር ዘይት፣ 14 ሊትር የባትሪ ውሃ የዋናው መ/ቤት ተሽከርካሪዎች

እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን፤ ለተሰጠው አገልግሎትም ክፍያው ለማደያዎች በወቅቱ እንዲከፈል ተደርጓል፡፡

- በሌላ በኩል መ/ቤቱ በገባው ውል መሠረት በተለያዩ ምክንያት የተበላሹ 43 ተሽከርካሪዎች በመድህን ድርጅት ጥገናና ዕድሳት ተደርጎላቸው ወደ ምድብ ቦታቸው የተሠማሩ ሲሆን 4 ተሽከርካሪዎች በጥገና ሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡

## 16 የሕትመት ሥራን በተመለከተ

በ1999 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት ውስጥ ልዩ ልዩ የሕትመት ውጤቶች፣ መጠይቆች፣ መመሪያዎች የጥናት ሪፖርቶች፣ የመቀስቀሻ በራሪ ወረቀቶች፣ ካርታዎች የአስተዳደራዊ ደብዳቤዎች፣ ቅጾች፣ ዶክመንቶች የሂሳብ ሰነዶችና ሌሎችም የተጠየቁ የሕትመት ሥራዎች በ62,353 ጥራዞችና በ12,982,795 ገጾች ታትመዋል፡፡

## 17 ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች

### 17.1 የሴቶች ጉዳይን በሚመለከት

- መ/ቤቱ ከዚህ በፊት በነበረው መዋቅር የሴቶችን ጉዳይ የሚመለከት የሥራ ክፍል አልነበረውም፡፡ ሆኖም አዲሱ መዋቅር ላይ የሥራ ክፍሉ እንዲኖር በመደረጉ መዋቅሩ ተጠናቆ ሠራተኞች ለሥራ ክፍሉ በቋሚነት እስኪመደቡ ድረስ ጊዜያዊ የሴቶች ጉዳይ መምሪያ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

- ይህ የተቋቋመው መምሪያም በመዋቅሩ መሠረት የሚመደቡ የክፍሉ ሠራተኞችን ሊያሠራ የሚችል የዓመቱን የሥራ ዕቅድና መረሃ-ግብር አዘጋጅቷል፡፡

- ከሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የተላከ አንድ መጠይቅ ተሞልቶ ለጠያቂው መ/ቤት የተላከ ሲሆን፤ የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴርን አጠቃላይ ዕቅድ ለማዕደቅ በተደረገ የግማሽ ቀን ሴሚናር ላይ መ/ቤቱ ተሣትፎ አድርጓል፡፡

- የመ/ቤቱን የሴቶች ጉዳይ የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎችን ለጠያቂዎቹ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

### 17.2 የኤች. አይ .ቪ. /ኤድስን በሚመለከት/

- በአስፈፃሚ. መ/ቤቶች የራሣቸው /የኤች.አይ.ቪ./ ኤድስ መከታተያ ግብረሃይል እንዲያቋቁሙ በመንግሥት በተሰጠ መመሪያ መሠረት በኤጀንሲው ውስጥ መመሪያው በሚያዘው መሠረት አንድ ግብረ-ሃይል ተቋቁሟል::

- ይህ ግብረ-ሃይል የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስን በተመለከቱ ተግባራትን በኤጀንሲው ውስጥ ለማከናወን እንዲችል ለማድረግ የራሱ የሆነ መረሃ-ግብር አዘጋጅቷል::

- ፈቃደኛ የሆኑ የኤጀንሲው መ/ቤት ሠራተኞች በየወሩ ከደመወዛቸው የተወሰነ ገንዘብ እያሰባሰቡ ለተስፋ ጉህ ማህበር ገቢ እያደረጉ ይገኛሉ:: እንዲሁም ከማኀበሩ ጋር በመተባበር ለመ/ቤቱ ሠራተኞች በኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ላይ የሚያተኩር ድራማ እንዲያዩ ተደርጓል::

- ለ3ኛው ዙር አገር አቀፍ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ በተዘጋጁ ፖስተሮች ላይ ስለኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ግንዛቤ የሚሰጡ ጽሑፎች እንዲወጡ ለማድረግ በዝግጅት ላይ ይገኛል::

- ኤጀንሲው ሁለት ኤች.አይ.ቪ. /ኤድስን የተመለከቱ ጥናቶችን ከሌሎች መ/ቤቶች በተገኘ የበጀትና የቴክኒክ ድጋፍ አካሂዷል::

## 18 ያጋጠሙ ችግሮችና የተሰጡ መፍትሄዎች

- በክልሎቹ የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ ከተከናወነ በኋላ በየወቅቱ አዳዲስ የአስተዳደር ዕርከኖች በመዋቀራቸው ምክንያት በወረዳዎችና በቀበሌዎች ተከናውኖ የነበረው የቆጠራ ካርታ እንደገና እንዲሰራ ተደርጓል:: ለዚህም ተጨማሪ ወጪ፣ ጊዜና የሰው ኃይል ጠይቋል:: ቢሆንም ከጥቅምት ወር 1999 ጀምሮ ይህ የማስተካከልና አዳዲስ የቆጠራ ቦታ ካርታ የመሥራት ሂደት ተከናውኗል::

- ለኤጀንሲው በጊዜያዊነት (ለሁለት ዓመት ተኩል) የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ቢሮ ተሰጥቶታል:: ቢሮው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ሥራን በተረጋጋ ሁኔታ ለመሥራትና ለመምራት ይረዳል:: ሆኖም ዘላቂ መፍትሄው ኤጀንሲው የራሱ የሆነና በቂ ቢሮ ያለው ሕንፃ ሲገነባ ብቻ ነው:: በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ ከሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር የሚገነባውን የቢሮ ዲዛይን የተዘጋጀ ሲሆን፤ በተጨማሪም ለግንባታ የሚሆን ቦታ ለአዲስ አበባ ባለአደራ አስተዳደር ጠይቆ ምላሽ እየተጠበቀ ይገኛል:: በመሆኑም ሁሉም አካላት ለሚጠይቁት ትብብር አፋጣኝ መልስ እንዲሰጡ ከወዲሁ እንጠይቃለን::